# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የኢትዮጵያ ደን ልማት

# ከ2016-2018 በጀት ዓመት የሶስት ዓመት ዕቅድ

መጋቢት 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ማውጫ

1. መግቢያ ..... 3

2. የተቋሙ ርዕይ፣ ተልዕኮ እና ዕሴቶች ..... 6

3. የባለፉት ሶስት ዓመታት (2013-2015) የልማት ዕቅዱ አፈፃፀም ግምገማ ..... 7

4. የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) የልማት ዕቅድ እንድምታዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች 18

4.1. የደን ሃብት ይዞታ እና ጥቅሞች ..... 20

4.4. ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂክ ግቦች ..... 23

4.4.1. ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ..... 23

4.4.2. ስትራቴጂካዊ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት ..... 24

ግብ 1፦ የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ ..... 25

5. በዕቅድ ዘመኑ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአደጋ ስጋቶች እና የመቋቋሚያ ስልቶች ..... 36

6. የዘርፉ ዕቅድ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ..... 38

8. ማጠቃለያ ..... 41

9. አባሪ ..... 42

## 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዎ ሪፐብሊክ መንግስት ሀገራዊ ርዕይ በሕዝብ ተሳትፎና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር የሰፈነባት፣ ማህበራዊ ፍትሕ የነገሰባት፣ ከድህነት ተላቃ በ2030 የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ሀገር እንድትሆን ማድረግ ነው፡፡ ይህን ርዕይ ለማሳካት የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ልማት ዕድገት የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ትግበራን መሠረት ያደረገ እና ዘላቂና አስተማማኝ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ መንግስት በ2004 ዓ.ም. በማዘጋጀት ወሳኝ የልማት አቅጣጫዎችን ቀይሶ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡

ለአየር ንብረት ለዉጥ የማይበገር አረንጓዴ ስትራቴጂ ለይቶ ካስቀመጣቸው አራት ዋና ዋና ምሰሶዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የደኑ ዘርፍ ነው፡፡ የደኑ ዘርፍ ዋነኛ ምሰሶ የሆነበትም ምክንያት በሀገራችን በፈጣን ሁኔታ በማደግ ላይ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ልማት ደህንነትና ዘላቂነት ለማረጋገጥ መንግስት ከሁሉም ሴክተሮች ወደ አየር በሚለቀቁ በካይ ጋዞች ምክንያት የሚመጣውን የአየር ብክለት ለመቀነስ የደኑ ዘርፍ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው በመታመኑ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በሀገራችን ለደኑ ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው በቢሊዮን የሚቆጠሩ የደን ችግኞች በየአመቱ እንዲተከሉ በማድረግ፣ ትኩረት የተሰጣቸውን የተፈጥሮ ደኖች በመንከባከብ እና በመጠበቅ፤ የተራቆቱ አካባቢዎች በተደራጀ የህዝብ ተሳትፎ እንዲያገግሙ በማድረግ የሀገራችንን የደን ሽፋን ለመጨመር የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ በየክልሉ ተሳትፎአዊ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በተደራጀ የሕዝብ ንቅናቄ ርብርብ ተደርጎ በመሰራቱ ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ ተራቁተው የነበሩ አካባቢዎች አፈራቸውና እርጥበታቸው በመመለሱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ዕፅዋቶች በማልማት ተራራዎች የሃብት ምንጭ መሆን ጀምረዋል፡፡

ወደ አየር በሚለቀቁ በካይ ጋዞች ምክንያት የሚመጣውን የአየር ብክለት ከመቀነስ ባሻገር የሀገራችንን የደን ልማት በማስፋፋት የሕዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ የሥርዓተ-ምህዳር ቀጠናዎችን ሚዛን እንዲጠበቅ ለማድረግና በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የራሱን ድርሻ እንዲያበረክትና በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚደርሰውን የድርቅ እና የጎርፍ

አደጋ በአስተማማኝ ደረጃ ለመቋቋም የደን ሃብት ቁልፍ ሚና እንዳለው በልማት ፖሊሲዎቻችንና ስልቶቻችን ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

የደኑ ዘርፍ በቤተሰብ እና በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የራሱን ድርሻ እንዲያበረክት ከማድረግ አንጻር እያደገ የመጣውን የህብረተሰቡን የደን ምርት ውጤት ፍላጎትን ለሟሟላት፣ ለቤተሰብ ፍጆታ እና ተጨማሪ የጥሬ ገንዘብ ለማስገኘት፤ ከውጪ የሚገቡ የተለያዩ የደን ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት፣ በደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀም እና በተለያየ ደረጃ ባሉ የደን ኢንድስትሪዎች ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም ወደ ውጪ የሚላኩ የደን ውጤቶችን በማምረት እና ወደ ውጪ በመላክ ሀገራችን የውጭ ምንዛሬ ከዘርፉ እንድታገኝ ሲደረግ ቆይታል፡፡ የደኑ ዘርፍ ለሃገራችን አጠቃላይ የሃገር ውስጥ ምርት (GDP) እስከ 12.8 ፐርሰንት ድርሻ እንዳለው ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም የደኑ ዘርፍ ለግብርና፣ ለኢነርጂ፣ ለውሃ፣ ለጤና፣ ለቱሪዝም ወዘተ እያበረከተ ያለው ግልጋሎት ከፍተኛ ነው፡፡ በአጠቃላይ በሀገራችን እየተሰሩ ያሉ የደን ልማት፣ እንክብካቤ እና ጥበቃ ስራዎች በአለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃ የሀገራችንን መልካም ገጽታና የተሰሚነት ደረጃ ከፍ እንዲል አስችሏል፡፡

በዚሁ መሰረት የሁለተኛዉ ዙር የአምስት ዓመት (2008-2012) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተዘጋጅቶ ሲተገበር ቆይቷል፡፡ የኢትዮጲያ የደን ልማት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግቦችን ከአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ጋር ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ለማስቻል የተለያዩ አዋጆች፣ መመሪያዎች እና መርሃ ግብሮችን በማዘጋጀት፤ የቴክኖሎጂ ፍላጎትና የፋይናንስ ምንጮችን በመለየትና ድጋፍ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶችን ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በማዘጋጀት፤ በዘርፎችና በባለድርሻ አካላት እንዲፈጸሙ በመደገፍና ሂደቱን በማስተባበር የተገኘው ሃብት በየደረጃው ለስትራቴጂዉ ትግበራ እንዲዉል ተደርጓል፡፡

ስለሆነም ይህ የኢትዮጵያ የደን ልማት ቀጣይ አስር ዓመት (2013-2022 ዓ.ም) መሪ የልማት ዕቅድ ያለፉትን ዓመታት አፈጻጸም በመገምገም ከነበሩት የአፈጻጸም ጥንካሬዎችና ጉድለቶች ትምህርት በመውሰድ በዚህ ዕቅድ ዘመን የዘርፉን የተሻለ የማስፈጸም አቅም በመፍጠር የተቀመጡ አቅጣጫዎችና ለቀጣይ አስር ዓመት የሚደረስባቸዉን ግቦች ከሀገራዊ የልማት እድገት የትኩረት አቅጣጫዎች፣ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የተከለሰ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ (Updated NDC)፣ ሀገራዊ የረጅም ጊዜ ዝቅተኛ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት የልማት ስትራቴጂ (Long Term Low Emissions Development

Strategy/ LT_LEDS)፣ ከዘላቂ የልማት ግቦች፣ ከአፍሪካ አጀንዳ 2063፣ ሀገራችን የፈረመቻቸዉ አለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች (Multilateral Environmental Agreements- MEAs) የትግበራ ደረጃ እንዲሁም ከዘርፉ አለም አቀፍ፣ አህጉራዊና ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማስተሳሰርና በማጣጣም የዘመኑን ዕቅድ ስኬታማ ለማድረግ ይሰራል። የተዘጋጀውን የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ስኬታማ ለማድረግ ዓመታዊ ዕቅድና የድርጊት መርሐግብር በማዘጋጀት፣ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር የሚኖረንን መደጋገፍ በማጠናከር እንዲሁም የአፈጻጸም ደረጃ በመገምገም፣ ክፍተቶችን በመለየትና በማሻሻል ስኬታማ ለማድረግ ይሰራል።

ይህ ሠነድ እንዲዘጋጅ መነሻ የሆነው በዋነኛነት የፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የደን ልማት እና የደን ምርምር በአዲስ መልክ የኢትዮጵያ ደን ልማት ሆኖ እንዲደራጅ በመደረጉ፣ በአንድ ላይ የተደራጁት ተቋማት ቀደም ሲል የነበራቸውን የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ የተጣጣመ አንድ ወጥ ሰነድ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ነው። በመሆኑም የልማት ዕቅዱ በ2014 የዕቅዱ መነሻ ሁኔታዎችን፣ የተቋሚቱን የሁለተኛ ዙር የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ፣ በዕቅድ ዘመኑ የሚከናወኑ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራትን እና ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልግ የሰው ኃይልና ማስፈፀሚያ በጀት፣ እንዲሁም አፈፃፀሙን ለመከታተል የሚያግዝ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት፣ እንዲይዝ ተደርጎ የተዘጋጀ ሰነድ ሲሆን ዝርዝር ዕቅዱ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 2. የተቋሙ ርዕይ፣ ተልዕኮ እና ዕሴቶች

### ርዕይ

በ2022 ዓ.ም. ዘላቂ ደን ልማት፣ አያያዝና አጠቃቀምን በማረጋገጥ በአፍሪካ የላቀ የደን ልማት ተቋም ሆኖ መገኘት፡፡

### ተልዕኮ

የደን ሀብታችን በዘላቂነት እንዲጠበቅ፣ እንዲለማ፣ የተራቆቱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ እና የደን ውጤቶችን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ አገራችን ከደን ሀብት የተሻለ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊ እና ስርዓተ-ምህደራዊ ጠቀሜታን እንድታገኝ በማድረግ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን በመቋቋም ለሁለንተናዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ፡፡

### እሴቶች

- ግልጸኝነት
- ቁርጠኝነት
- አጋርነት
- ጥራት
- ቅልጥፍና
- ውጤታማነት
- የሙያ ስነ-ምግባር
- ፈጠራ

## 3. የባለፉት ሶስት ዓመታት (2013-2015) የልማት ዕቅዱ አፈፃፀም ግምገማ

የደን ሀብት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችና ግልጋሎቶች አሉት። ይህንን ግልጋሎት ከማሳደግ አንፃር ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል።

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ የሚጠበቁ ውጤቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈፀም እንዲያስችል በየበጀት ዓመቱ ያለፈውን ዓመት አፈፃፀም በማዕከላትና በዋናው መስሪያ ቤት በሚገኙ አመራሮችና በክልል ባለድርሻ አካላት እንዲገመገም በማድረግና አስፈላጊ ግብዓቶች በመውሰድ በየዓመቱ ዕቅድ ዝግጅት ላይ ግብዓቱ እንዲካተት በማድረግ የተዘጋጀውን ዕቅድ በማኔጅመንት እንዲሁም በባለድርሻ አካላት እንዲገመገምና ለሰራተኞች ተዋውቆ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል። ከዚህም በተጨማሪ ለስራው አስፈላጊ ግብዓቶችን የማሟላት፣ ስራዎችን የሚያሳልጡ የአሰራር ስርዓቶችን የመዘርጋትና የማጠናከር እንዲሁም የተቋም አደረጃጀት ተከትሎ በመሰራት ላይ ያለውን የመስሪያ ቤቱን መዋቅር ከዳር ለማድረስ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል።

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ለደን ልማት እና ምርምር እንዲሁም ለአቅም ግንባታ ስራዎች 28,241,250 USD ከተለያዩ አጋር አካላት ማግኘት ተችሏል። እንዲሁም ከዛፍ ዘር ሽያጭ 496,390 ብር ተገኝቷል።

በተደረገው የደን ልማትና ጥበቃ ስራ ከደን ዘርፍ 8 ሚ/ን ቶን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ለመቀነስ ታቅዶ 13.1756 ሚ/ን ቶን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት መቀነስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100 % በላይ ሆኗል። አፈፃፀሙ ከዕቅድ በላይ የሆነበት ምክንያት ባለፉት ዓመታት በተደረገ የተጠናከረ የደን ተከላና ጥበቃ ስራዎች ነው።

በደን ልማት፣ በደን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እንዲሁም በደን ጥበቃ እና አጠቃቀም ህጎች ዙሪያ ለ2.05 ሚሊየን የማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመስጠት ታቅዶ ለ2.643 ሚሊየን የማህበረሰብ ክፍሎች በስልጠናና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ሆኗል።

2.4 ሚ/ሄ/ር የተከላ መሬት ለመለየት ታቅዶ በ2.944 ሚ/ሄ/ር ከ100% በላይ መለየት ተችሏል፣ 10.67 ቢሊዮን ደረጃቸውን የጠበቁ ችግኞች ተፈልተው እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ 10.168 ቢሊዮን (የዕቅዱን 95.29%) የደን ችግኞች መትከል ተችሏል። የቀርቀሃ ደን ሽፋን 0.06 ሚ/ሄ/ር ለማድረስ 0.16 ታቅዶ ሚ/ሄ/ር ማድረስ የተቻለ ሲሆን

አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ለቀርከሀ ልማት የተሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑና ከመደበኛ በተጨማሪ የፕሮጀክቶችና የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ 2.2 ሚ/ሄ/ር የተራቆቱ የደን መሬቶችን በመለየት እንዲያገግሙ ለማስቻል ታቅዶ 1.977 ሚ/ሄ/ር የተራቆቱ የደን መሬቶችን በመለየት እንዲያገግሙ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 89.86% ሆኗል፡፡

በየበጀት ዓመቱ 18.678 ሚሊዮን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በየዓመቱ 18.678 ሚሊዮን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ሆኗል፡፡
2.28 ሚሄ/ር የተፈጥሮ ደን በአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን እንዲታቀፉ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ከሮያሊቲ እና ከተወረሱ የደን ምርት ውጤቶች ሽያጭ 510 ሚሊየን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በተሰራው ስራ 665.7 ሚሊየን ብር የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ 100% በላይ ሆኗል፡፡ ከእቅድ በላይ የተከናወነበት ምክንያት የተሻለ ክትትልና ድጋፍ በመደረጉ እና ክልሎችም ትኩረት ስለሰጡት ነው፡፡ በተመሳሳይ በምርምሩ ዘርፍ የውስጥ ገቢን ጨምሮ ከአጋር አካላት በተገኘ ድጋፍ 2.4 ሚሊዮን ብር ማግኘት ተችሏል፡፡

ከ 2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ለ870,000 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በደን ጥበቃ፤ የደን ምርቶችን በመጫን፤ በማጓጓዝና በማውረድ፤ በችግኝ ተከላና እንክብካቤ፤ በእንጨት ኢንዱስትሪ፤ ኢንተርፕራይዞችና ማህበራትን በማደራጀት፤ የደን ምርት ውጤቶችን በማቅረብ፤ በመቸርቸርና በመላክ ፤በከሰል ማክሰል (አማራ ክልል) እና የመሳሰሉት የስራ መስኮችን በአጠቃላይ ለ 800,000 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 92% ነው፡፡
ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ 2.38 ሚልዮን ቶን የደን ምርት ውጤቶች ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በዕቅድ ተይዞ ክንውን 5.038 ሚልዮን ቶን (ከዚህ ውስጥ 25,000 ቶን ለውጭ ገበያ የቀረበ) ሲሆን አፈፃፀሙ ከ100% በላይ ነው፡፡

አፈፃፀሙ ከዕቅድ በላይ የሆነበት ምክንያት በዘርፉ  የደን ውጤት ምርት ፍላጎት እና አቅርቦት እየጨመረ በመምጣቱ ነው፡፡

ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ተቋሙ በምርምር ዘርፍ የደን ሽፋን ለመጨመር ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የደን ውጤቶችን ምርታማነት ለማሳደግ፣ እሴት ለመጨመርና የገበያ ስርዓትን ለመዘርጋት እና ስርዓተ-ምህዳሩን ለማሻሻል የሚያስችሉ በሰዉ ሰራሽ ደን፣ በደን ዉጤቶች ኢኖቬሽን፣ በፖሊሲና ሶሺዮ-ኢኮኖሚክስ፤ በተፈጥሮ ደን እና በአየር ንብረት ለወጥ የተለያዩ የምርምር ፕሮጀክቶችን ነድፎ መረጃና ቴክኖሎጂዎችን በማዉጣት የበኩሉን ሀገራዊ ሃላፊነት ሲወጣ ቆይቷል፡፡ በዝርዝር ስንመለከት ከ2013 እስከ 2015 በጀት ኣመት አጋማሽ ድረስ በሰው ሰራሽ ደን ምርምር 34 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 21 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 61.8%፣ በተፈጥሮ ደን እና አየር ንብረት ለዉጥ 43 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 47 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 100%  በላይ የደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር 32 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት ታቅዶ 27 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 84.4% እና በፖሊሲና ሶሺዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር 11 መረጃ ለማዉጣት ታቅዶ 10 ማዉጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 90.9% ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ያለዉን የስራ ክንዉን ስንመለከት በምርምሩ ዘርፍ 120 የምርምር ውጤቶችን (100 መረጃዎች 20 ቴክኖሎጂዎች) ለማውጣት ታቅዶ 105 የምርምር ውጤቶችን (95 መረጃዎች 10 ቴክኖሎጂዎች)  ለማውጣት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 87.5 % ነው፡፡ የቴክኖሎጂ ቅድመ ማስፋትን በተመለከተ ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ ለ470 ከተለያዩ አካላት ለተዉጣጡ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ466 ተጠቃሚዎች ማሰልጠን የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 99.1% ነዉ፡፡

በአጠቃላይ 2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት አጋማሽ ድረስ በተሰሩ ስራዎች የፊዚካል ስራዎች አፈፃፀም 93.5% ሲሆን፣ ለተቋሙ ከተለቀቀው መደበኛ በጀት 749,840,583.40 ብር ውስጥ 574,567,617.85 ብር ጥቅም ላይ ለማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 76.6 % ነው፡፡ አፈፃፀሙም ያነሰበት ምክንያት በዋናነት በሃገር ደረጃ በተከሰተው የግንባታ ማቴሪያል የዋጋ መናር እና በገበያ ላይ የግንባታ ማቴሪያል እጥረት ሳቢያ የሁለቱ ላቦራቶሪዎች የግንባታ ስራዎች በመዘግየታቸው ነው፡፡ ይህንም ችግር ለመቅረፍ ከተቋራጭ ድርጅቶቹ ሃላፊዎች፣ ከአማካሪው ድርጅት አመራሮች፣ ከግንባታ ቁጥጥር ባለስልጣን ባለሙያዎች፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አመራሮች ጋር በመነጋገር የዋጋ ለውጥ በግንባታ

ላይ ያስከተለውን ችግር እንዴት መቅረፍ እንደሚቻል ውይይት ተደርጓል፡፡ ለመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ቀርቦ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ በቀጣይ የግንባታው ስራ እንዲፋጠን ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

## በአፈፃፀም ሂደት ያጋጣሙ ችግሮችና የተወሰዱ/ሊወሰድ የሚገባቸው የመፍትሔ ርምጃዎች

### ያጋጠሙ ችግሮች

- በክልሎችና ከዚያ በታች ባለ የአስተዳደር እርከን ወጥና የተጠናከረ መዋቅራዊ አደረጃጀት አለመኖር፣
- የተሟላ ሪፖርት ከክልሎች በወቅቱና ጥራት ባለው ደረጃ ማግኘት አለመቻል፣
- በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት እየጨመረ የመጣ የደን እሳት፣ የደን ተባይና በሽታ ክስተት፣
- የፀጥታ ችግር፣
- በCOVID-19 ወረርሺኝ ምክንያት የልማትና ምርምር ስራዎች በሚጠበቀው ደረጃ መፈፀም አለመቻሉ፤
- የምርምርና የልማት ስራዎችን ለማከናወን የበጀት ዕጥረት መኖሩ፣
- በግንባታ ዕቃዎች ዕጥረትና ዋጋ መናር ምክንያት ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መጠናቀቅ አለመቻላቸው፡፡
- የልማት አጋር አካላት ድጋፍ በተጠበቀው ደረጃ አለመሆን፣

### የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

- ባለው ውሱን በጀት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ስራዎች በመለየት መስራት፣
- የዋጋ ማሻሻያ እንዲፈቅድልን የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ተጠይቆ የፈቀደልን ሲሆን በቀጣይ የዋጋ ማሻሻያው ተግባራዊ ሲደረግ የግንባታ አፈፃፀሙ የሚሻሻል ይሆናል፡፡

## ሰንጠረዥ 2. የ2013 እስከ 2015 የ3 ዓመት ዘርፉ ልማት ዕቅድ አፈፃፀም በቁልፍ አፈጻጸም አመልካቾች (ከ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ አንፃር)

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብ 1. የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ያደገ የተገልጋይ እርካታ | በመቶኛ | 80 | 100 | 86 | 81.2 | 94.4 | 88 | 84 | 95 | 90 | 86 | 84 | 97.6 | 86 | 84 | 97.6 |
| ግብ 2. የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ጥቅም ላይ የዋለ በጀት ድርሻ | በመቶኛ | | 100 | 100 | 88.4 | 88.4 | 100 | 91.9 | 91.9 | 100 | 100 | 91 | 91 | 100 | 90.43 | 90.43 |
| የተደረገ የውስጥ ኦዲት ክትትል | በቁጥር | 4 | 40 | 4 | 4 | 100 | 4 | 3 | 75 | 4 | 2 | 2 | 100 | 10 | 9 | 90 |
| የኦዲት ግኝቶች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ የማስተካከያ መርሃ ግብር | በቁጥር | 1 | 10 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 1 | 100 | 3 | 3 | 100 |
| ግብ 3. የሀብት ግኝትን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ከአጋር ሀገሮች እና ድርጅቶች የተገኘ የፋይናንስ ድጋፍ | በሚሊየን ዶላር | | 200 | 50 | 302.23 | 100 | 20 | 138.2 | 100 | 20 | 20 | 28.2 | 100 | 90 | 468.63 | 100 |
| ግብ 4 ፦ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል | | | | | | | | | | | | | | | | |
| ከደን ዘርፍ የቀነሰ የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት መጠን | በሚ/ሜ/ቶን | 10.9 | 120 | 3 | 2.8 | 93.3 | 5 | 10.02 | 100 | 7 | | 0.3556 | | 8 | 13.1756 | 100 |
| ተሳትፎ የተደረገባቸው አለም አቀፍ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ መድረኮች | ቁጥር | 1 | 20 | 2 | 2 | 100 | 2 | 2 | 100 | 2 | 1 | 2 | 100 | | | |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብ 5. የደን ህግ ተከባሪነት ማረጋገጥ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የተዘጋጁ የደን ህግ ማዕቀፎች | በቁጥር | | 7 | | | | | | | 4 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| በደን ህጎች እና አፈፃፀም ላይ ግንዛቤ ያገኙ የህብረተሰብ ክፍል ብዛት፣ | በሚሊዮን ቁጥር | | 20.05 | 2 | 2.1 | 100 | 0.05 | 0.439 | 100 | 2.5 | | 0.104 | | 2.05 | 2.643 | 100 |
| የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው በደን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ብዛት | በቁጥር | 659 | 1240 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 400 | 200 | 246 | 100 | 400 | 446 | 100 |
| ግብ 6 ፡- አገራዊ የደን ሽፋንን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የዛፍ ዘር ማሰባሰብና ማሰራጨት | ቶን | 1958.59 | 3500 | 300 | 451.16 | 100 | 325 | 504.83 | 100 | 325 | 150 | 293.1 | 100 | 775 | 1249.32 | 100 |
| በደን የተሸፈነ መሬት ድርሻ | በመቶኛ | 15.5 | 30 | 17 | 17.2 | 100 | 18.5 | 17 | 91.9 | 20 | | | | 18.5 | 17 | 91.9 |
| የተዘጋጁ የዛፍ ችግኞች | ቢ/ቁጥር | 18.735 | 40 | 4 | 6.52 | 100 | 4 | 3.799 | 95 | 3 | 0.25 | 2.763 | 100 | 8.25 | 10.67 | 100 |
| የተጠበቀ ነባር፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ደን (ከደን እሳት፣ ከተባይና በሽታ፣ ከመጤ ወራሪ አረም፣ ከህገወጥ ምንጣሮ እና መመናመን) | በሚ/ሄ/ር | 17.2 | 33.12 | 17.2 | 19.47 | 100 | 18.68 | 18.68 | 100 | 18.6 8 | 18.68 | 18.68 | 100 | 18.68 | 18.68 | 100 |
| ተከላ የተካሄደበት መሬት ስፋት | በሚ/ሄ/ር | 6.057 | 8 | 1 | 0.7718 | 77.2 | 0.8 | 0.716 | 89.5 | 0.6 | 0.6 | 0.748 | 100 | 2.4 | 2.944 | 100 |
| ያገገመ የተራቆተ የደን መሬት | በሚ/ሄ/ር | 3.9684 | 11 | 0.95 | 0.694 | 73.1 | 1 | 0.692 | 69.2 | 1 | 0.25 | 0.591 | 100 | 2.2 | 1.977 | 89.86 |
| የቀርከሀ ደን ማልማት | በሚ//ሄ/ር | | 0.2 | 0.02 | 0.0147 | 73.5 | 0.02 | 0.0675 | ›100 | 0.02 | 0.02 | 0.077 | 100 | 0.06 | 0.16 | 100 |
| የጥምር ደን ግብርና ስራ እንዲጎለብት የተደረገበት የመሬት ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | | 1 | | | | | | | 0.1 | | 0.058 7 | | | 0.0587 | |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀገራዊ የደን ሀብት ቆጠራ ማካሄድ | በመቶኛ | | 100 | | | | 50 | 15 | 30 | 100 | 10 | 10 | 100 | 60 | 25 | 41.67 |
| የደን ሽፋን መረጃ | በቁጥር | 1 | 5 | 1 | 1 | 100 | | | | | | | | 1 | 1 | 100 |
| የተዘጋጀ የደን ማኔጅመንት ፕላን | በሚ/ሄ/ር | 1.164 | 2 | 0.2 | 0.195 | 97.41 | 0.2 | 0.97 | 96.87 | 0.2 | | | | 0.4 | 1.165 | 100 |
| የደን አያያዝ የተሻሻለላቸው የከተሞች ብዛት | በቁጥር | 18 | 50 | 11 | 9 | 81.82 | 5 | 5 | 100 | 5 | 3 | 4 | 100 | 19 | 18 | 94.74 |
| ግብ 7. የደን ሀብት ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ማሳደግ፣ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የደን ዘርፍ ለሀገራዊ ምርት የሚያበረከክተውን ድርሻ | በመቶኛ | 4 | 8 | | | | | | | | | | | | | |
| ነባር የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 2 | 4.62 | 2 | 2 | 100 | 2.12 | 2.283 | ›100 | 2 | 2.16 | 2.28 | 100 | 1.28 | 2.28 | 100 |
| አዲስ የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | | 3.03 | 0.2 | 0.202 | 100 | 0 | | | 0.2 | | 0.0525 | | 0.2 | 0.2545 | 100 |
| ከሰው ሰራሽ ደንና ከደን ተረፈ ምርቶች በተሻሻለ ዘዴ የተመረተ ከሰል መጠን | ሚሊ/ቶን | 0 | 2 | 0.2 | 0.2014 | 100 | 0.2 | 0.345 | 100 | 0.2 | 0.067 | 0.152 | 100 | 0.467 | 0.6984 | 100 |
| ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የቀረበ የደን ምርት መጠን | ቶን (ሚሊዮን) | 0.16225 | 10.2 | 1.02 | 1.964 | 100 | 1.02 | 2.134 | 100 | 1.02 | 0.34 | 0.94 | 100 | 2.38 | 5.038 | 100 |
| በደን ዘርፍ ስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ብዛት | በሚሊዮን ቁጥር | 1.3 | 2.5 | 0.5 | 0.349 | 70 | 0.25 | 0.255 | 100 | 0.25 | 0.12 | 0.196 | 100 | 0.87 | 0.8 | 92.0 |
| ሥርዓተ ምህዳሮች የሚያመነጩትን አገልግሎት ዋጋ ትመና የሚያሳይ መረጃ፣ | በቁጥር | | 4 | 3 | 3 | 100 | 1 | 1 | 100 | 1 | | | | 4 | 4 | 100 |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀ ም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀ ም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ከደን ሮያሊቲ የተገኘ ሀብት መጠን | በቢሊዮን ብር | 0.636 | 2.8 | 0.2 | 0.258 | 100 | 0.2 | 0.293 | 100 | 0.25 | 0.11 | 0.1147 | 100 | 0.51 | 0.6657 | 100 |
| ከደን ምርት ኤክስፖርት የተገኘ እና በሃገር ውስጥ የደን ምርት ምክንያት የዳነ የውጭ ምንዛሪ መጠን | በሚሊዮን ዶላር | 6 | 278 | 20 | 12 | 60.15 | 20 | 2.442 | 12.2 | 26 | 7 | 7.682 | 100 | 47 | 22.124 | 47.1 |
| ግብ 8. የደን መረጃና ቴክኖሎጂ ማመንጨትና ማላመድ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| በምርምር የወጡ ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች | | 237 | 429 | 63 | 62 | 98.4 | 50 | 37 | 74 | 43 | 7 | 6 | 85.7 | 120 | 105 | 87.5 |
| በሰው ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን | በቁጥር | | 163 | 12 | 8 | 66.7 | 22 | 13 | 59 | 15 | | | | 34 | 21 | 61.8 |
| በተፈጥሮ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ | በቁጥር | | 98 | 30 | 36 | 100 | 9 | 9 | 100 | 13 | 4 | 2 | 50 | 43 | 47 | 100 |
| በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን | በቁጥር | | 110 | 16 | 13 | 81.3 | 13 | 10 | 77 | 9 | 3 | 4 | 100 | 32 | 27 | 84.4 |
| ፖሊሲና ሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር | በቁጥር | | 58 | 5 | 5 | 100 | 6 | 5 | 83.3 | 6 | | | | 11 | 10 | 90.9 |
| ግብ 9. የመረጃና ቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የተዘጋጁ የምርምር ውጤቶች የትግበራ ፓኬጅ ብዛት | | | 328 | 34 | 34 | 100 | | | | 41 | | | | 34 | 34 | 100 |
| በሰው ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን | በቁጥር | | | | | | | | | 13 | | | | | | |
| በተፈጥሮ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ | በቁጥር | | | | | | | | | 13 | | | | | | |
| በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን | በቁጥር | | | | | | | | | 8 | | | | | | |
| ፖሊሲና ሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር | በቁጥር | | | | | | | | | 7 | | | | | | |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በታወቁ ጆርናሎች ላይ የታተሙ የምርምር ውጤቶች | በቁጥር | | 170 | | | | | | | 22 | | 7 | | | 7 | |
| በሰው ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን | በቁጥር | | | | | | | | | 9 | | 4 | | | 4 | |
| በተፈጥሮ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ | በቁጥር | | | | | | | | | 7 | | 1 | | | 1 | |
| በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን | በቁጥር | | | | | | | | | 3 | | | | | | |
| ፖሊሲና ሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር | በቁጥር | | | | | | | | | 3 | | 2 | | | 2 | |
| ለተጠቃሚዎች በቴክኖሎጂ ቅድመ ማስፋፋት የተሰጠ ስልጠና | በተሳታፊ ቁጥር | | 670 | 260 | 295 | 100 | 210 | 171 | 81.4 | 200 | | | | 470 | 466 | 99.1 |
| በተለያዩ የሚዲያ ቻናሎች እተደራሽ የተደረገ መረጃ ብዛት | በቁጥር | | 96 | 24 | 24 | 100 | | | | 12 | | | | 24 | 24 | 100 |
| ግብ 10 የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሴቶች ድርሻ | በሚሊዮን ቁጥር | | 1.25 | 0.125 | 0.102 | 81.9 | 0.125 | 0.0723 | 57.8 | 0.063 | 0.0225 | 0.061 | 100 | 0.2725 | 0.2353 | 86.3 |
| የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ወጣቶች ድርሻ | በሚሊዮን ቁጥር | | | 0.125 | 0.197 | 100 | 0.125 | 0.12 | 96 | 0.125 | 0.15 | 0.1497 | 99.8 | 0.4 | 0.4667 | 100 |
| የተዘጋጀ የህፃናት ማቆያ | በቁጥር | | 8 | | | | | | | 2 | | | | | | |
| የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች አካቶ የተሰጠ ሥልጠናዎች ብዛት | በቁጥር | | 16 | | | | | | | 2 | 1 | | | | | |
| ግብ 11 ፦ የመሠረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል G+5 ላቦራቶሪ ግንባታ ስራ ያለበት ደረጃ | በመቶኛ | | 100 | | | | 30 | 15 | 50 | 100 | 40 | 23.6 | 59 | 40 | 23.6 | 59 |
| የደን ዉጤቶች እኖቬሽን ማዕከል ላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ G+3 ግንባታ ስራ ያለበት ደረጃ | በመቶኛ | | 100 | 45.68 | 16.96 | 37.1 | 100 | 40 | 40 | 100 | 60 | 44.19 | 73.6 | 60 | 45.13 | 75 |
| አውቶሜት የተደረጉ የተቋሙን አሰራሮች | በቁጥር | | 2 | | | | | | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| እንክብካቤ የተደረገላቸው ነባር የዛፍ ዘር ምንጮች | በሄ/ር | | 371 | 371 | 371 | 100 | 371 | 371 | 100 | 371 | 371 | 371 | 100 | 371 | 371 | 100 |
| አዲስ የተቋቋሙ የምርምር ችግኝ ጣቢያዎች ብዛት | በቁጥር | | 5 | | | | | | | 2 | 2 | 2 | 100 | 2 | 2 | 100 |
| በመካሄድ ላይ የሚገኙ የምርምር ችግኝ ጣቢያዎች ብዛት | በሄ/ር | | 8 | | | | | | | 8 | 8 | 8 | 100 | 8 | 8 | 100 |
| ግብ 12 ፦ የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የአጭር ግዜ ስልጠና ያገኙ ተመራማሪዎች | በቁጥር | - | | 53 | 53 | 100 | 76 | 76 | 100 | 164 | 164 | 86 | 51 | 293 | 215 | 73.4 |
| የረጅም ግዜ ስልጠና ያገኙ ሰራተኞች | | | | | | | 46 | | | 73 | 73 | 73 | 100 | 73 | 73 | 100 |
| የመጀመሪያ ዲግሪ | በቁጥር | | | | | | | | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| በሁለተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | | | | | 36 | | | 48 | 48 | 48 | 100 | 48 | 48 | 100 |
| በሶስተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | | | | | 10 | | | 24 | 24 | 24 | 100 | 24 | 24 | 100 |
| Post Doc | | | | | | | | | | | | | | | | |

| የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2012 | የ10 ዓመት ኢላማ | 2013 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2014 ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | 2015 ዕቅድ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% | ከ2013-2015 አጋማሽ ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸው የረጅም ግዜ ስልጠና ላይ ያሉ ሠራተኞች ብዛት | | | | 40 | 65 | 100 | 52 | | | 73 | 73 | 73 | 100 | 73 | 73 | 100 |
| የመጀመሪያ ዲግሪ | በቁጥር | | | | 1 | | 1 | | | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 |
| በሁለተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | | | 46 | | 26 | | | 48 | 48 | 48 | 100 | 48 | 48 | 100 |
| በሶስተኛ ዲግሪ | በቁጥር | | | | 17 | | 24 | | | 24 | 24 | 24 | 100 | 24 | 24 | 100 |
| Post Doc | በቁጥር | | | | 1 | | 1 | | | | | | | | | |
| ስልጠና ያገኙ አመራሮች ብዛት | ቁጥር | | 60 | | | | | | | 60 | 60 | - | 0 | | | |
| የተካሄደ የልምድ ልውውጥ ብዛት | በቁጥር | | 16 | 2 | 2 | 100 | | | | 2 | 2 | 2 | 100 | 4 | 4 | 100 |
| **አማካይ** | | | | | | | | | | | | | | | | 93.5 |

## 4. የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) የልማት ዕቅድ እንድምታዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች

ለአየር ንብረት ለዉጥ የማይበገር አረንጓዴ ስትራቴጂ ለይቶ ካስቀመጣቸው አራት ዋና ዋና ምሰሶዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የደኑ ዘርፍ ነው። የደኑ ዘርፍ ዋነኛ ምሰሶ የሆነበትም ምክንያት በሀገራችን በፈጣን ሁኔታ በማደግ ላይ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ልማት ደህንነትና ዘላቂነት ለማረጋገጥ መንግስት ከሁሉም ሴክተሮች ወደ አየር በሚለቀቁ በካይ ጋዞች ምክንያት የሚመጣውን የአየር ብክለት ለመቀነስ የደኑ ዘርፍ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው በመታመኑ ነው። በዚህም ምክንያት በሀገራችን ለደኑ ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸው በቢሊዮን የሚቆጠሩ የደን ችግኞች በየአመቱ እንዲተከሉ በማድረግ፣ ትኩረት የተሰጣቸውን የተፈጥሮ ደኖች በመንከባከብ እና በመጠበቅ፤ የተራቆቱ አካባቢዎች በተደራጀ የህዝብ ተሳትፎ እንዲያገግሙ በማድረግ የሀገራችንን የደን ሽፋን ለመጨመር የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። በየክልሉ ተሳትፎአዊ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በተደራጀ የሕዝብ ንቅናቄ ርብርብ ተደርጎ በመሰራቱ ምክንያት በከፍተኛ ደረጃ ተራቁተው የነበሩ አካባቢዎች አፈራቸውና እርጥበታቸው በመመለሱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ዕፅዋቶች በማልማት ተራራዎች የሃብት ምንጭ መሆን ጀምረዋል።

ወደ አየር በሚለቀቁ በካይ ጋዞች ምክንያት የሚመጣውን የአየር ብክለት ከመቀነስ ባሻገር የሀገራችንን የደን ልማት በማስፋፋት የሕዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ የሥርዓተ- ምህዳር ቀጠናዎችን ሚዛን እንዲጠበቅ ለማድረግና በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የራሱን ድርሻ እንዲያበረክትና በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚደርሰውን የድርቅ እና የጎርፍ አደጋ በአስተማማኝ ደረጃ ለመቋቋም የደን ሃብት ቁልፍ ሚና እንዳለው በልማት ፖሊሲዎቻችንና ስልቶቻችን ላይ በግልጽ ተቀምጧል። የደኑ ዘርፍ በቤተሰብ እና በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የራሱን ድርሻ እንዲያበረክት ከማድረግ አንጻር እያደገ የመጣውን የህብረተሰቡን የደን ምርት ውጤት ፍላጎትን ለሟሟላት፣ ለቤተሰብ ፍጆታ እና ተጨማሪ የጥሬ ገንዘብ ለማስገኘት፤ ከውጪ የሚገቡ የተለያዩ የደን ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች ለመተካት፣ በደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀም እና በተለያየ ደረጃ ባሉ የደን ኢንድስትሪዎች ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም ወደ ውጪ የሚላኩ የደን ውጤቶችን በማምረት እና ወደ ውጪ በመላክ ሀገራችን የውጭ ምንዛሬ ከዘርፉ እንድታገኝ ሲደረግ ቆይታል። የደኑ ዘርፍ ለሃገራችን አጠቃላይ የሃገር ውስጥ ምርት (GDP) እስከ 12.8 ፐርሰንት ድርሻ እንዳለው ጥናቶች ያመላክታሉ። በተጨማሪም የደኑ ዘርፍ ለግብርና፣ ለኢነርጂ፣ ለውሃ፣ ለጤና፣ ለቱሪዝም ወዘተ እያበረከተ ያለው ግልጋሎት

ከፍተኛ ነው። በአጠቃላይ በሀገራችን እየተሰሩ ያሉ የደን ልማት፣ እንክብካቤ እና ጥበቃ ስራዎች በአለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃ የሀገራችንን መልካም ገጽታና የተሰሚነት ደረጃ ከፍ እንዲል አስችሏል።

ከላይ የተጠቀሱትን ለማሳካትም በቀጣዩ የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) ዕቅድ የአስር ዓመት የልማት መሪ ዕቅድ መሰረት የተለያዩ የደን ልማትና ምርምር ስራዎች ይከናወናሉ። በዚህም መሰረት በሚደረገው የደን ልማትና ጥበቃ ስራ ከደን ዘርፍ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት በ33 ሚ/ን ቶን ለመቀነስ፣በደን ጥበቃ እና አጠቃቀም ህጎች ዙሪያ ለ7.5 ሚሊየን ለተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች ግንዛቤ ለመስጠት፣በደን የተሸፈነ መሬት ድርሻን 20 በመቶ ለማድረስ፣ በ2.4 ሚ/ሄ/ር መሬት ላይ ተከላ ለማካሄድ፣ 7.5 ቢሊዮን ደረጃቸውን የጠበቁ ችግኞች ለማዘጋጀት፣ የቀርቀሃ ደን ሽፋን 0.06 ሚ/ሄ/ር ለማድረስ፣ 3 ሚ/ሄ/ር የተራቆቱ የደን መሬቶችን በመለየት እንዲያገግሙ ለማድረግ፣በ22.24 ሚሊዮን ሄ/ር በሬት ላይ ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ፣0.6 ሚ/ሄ/ር ላይ የደን ማኔጅመንት ፕላን ለማዘጋጀት፣ነባር የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን 3.06 ሚሄ/ር ላይ እንዲታቀፉ ለማድረግ፣አዲስ የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን በ1.19 ሄክታር መሬት ላይ ተግባራዊ ለማድረግ፣ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የቀረበ የደን ምርት መጠን 6 ሚሊዮን ቶን ለማድረስ፣ከደን ሮያሊቲ የተገኘ ሀብት መጠን 900 ሚሊዮን ብር ለማድረስ፣ ከደን ምርት ኤክስፖርት የተገኘ እና በሃገር ውስጥ የደን ምርት ምክንያት የዳነ የውጭ ምንዛሪ መጠን 84 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት ፣እና ለ0.375 ሚሊዮን ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር እቅድ ተይዟል።

በተመሳሳይ በቀጣዩ የመካከለኛ ዘመን (2016-2018) ዕቅድ የአስር ዓመት የልማት መሪ ዕቅድ መሰረት የልማቱን ፍላጎት የሚያሟላ በዓይነትና በጥራት በቂ የቴክኖሎጂ እና የመረጃ አቅርቦት ይኖር ዘንድ በሰው ሰራሽ ደን ምርምር 48 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት፣ በተፈጥሮ ደንና አየር ንብረት ለዉጥ ምርምር 23 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት፣ በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር 34 መረጃና ቴክኖሎጂ ለማዉጣት እና በፖሊሲና ሶሺዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር 18 መረጃ ለማዉጣት በእቅድ የተያዘ ሲሆን በድምሩ 123 የደን ምርምር ቴክኖሎጂዎች እና መረጃዎች ለማውጣት፣ እንዲሁም አዳዲስና ነባር ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎችን ከተለያዩ አካላት ለተዉጣጡ ለ600 የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የህብረተሰብ ክፍሎች ለማስተዋወቅ እና ስልጠና ለመስጠት በእቅድ ተይዟል።

## 4.1. የደን ሃብት ይዞታ እና ጥቅሞች

ሀገራችን የተለያዩ የመሬት አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት እና በርካታ ተፈጥሮአዊ ስርዓተ ምህዳሮችን ያቀፈችና ይህንንም ተከትሎ የተለያየ የደን ሃብት፣ የዱር እንስሳትና የብዝሃ-ህይወት ባለቤት ስትሆን የደን ሽፋናችንም 19.2 ሚሊየን ሄ/ር (17.2%) ሆኖ በአራት የደን አይነቶች (Biomes) የተከፈለ ነው፡፡

ይህ የደን ሃብታችን በቤተሰብ እና በሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ የራሱን ድርሻ እያበረከተ ሲሆን እያደገ የመጣውን የህብረተሰቡን የደን ምርት ውጤት ፍላጎትን በሚሟላት፣ ለቤተሰብ ፍጆታ እና ተጨማሪ የጥሬ ገንዘብ በማስገኘት፤ ከውጪ የሚገቡ የተለያዩ የደን ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች በመተካት፣ በደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀም እና በተለያየ ደረጃ ባሉ የደን ኢንድስትሪዎች ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም ወደ ውጪ የሚላኩ የደን ውጤቶችን በማምረት እና ወደ ውጪ በመላክ ሀገራችን የውጭ ምንዛሬ ከዘርፉ እንድታገኝ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ የደኑ ዘርፉ ለሃገራችን አጠቃላይ የሃገር ውስጥ ምርት (GDP) እስከ 12.8 ፐርሰንት ድርሻ እንዳለውም ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር የደኑ ዘርፍ ለግብርና፣ ለኢነርጂ፣ ለውሃ፣ ለጤና፣ ለቱሪዝም ወዘተ እያበረከተ ያለው ግልጋሎት ከፍተኛ ሲሆን የደን ሃብታችን ወደ አየር በሚለቀቁ በካይ ጋዞች ምክንያት የሚመጣውን የአየር ብክለትን በመቀነስ እና የሥርዓተ- ምህዳር ሚዛን እንዲጠበቅ በማድረግ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚደርሰውን የድርቅ እና የጎርፍ አደጋ ለመቋቋም ቁልፍ ሚና አለው፡፡

ስለሆነም ከደን ሃብታችን የሚገኙትን ጥቅሞች በዘላቂነት ለማስቀጠል የተፈጥሮ ደኖቻችንን ለመጠበቅ፣ በሰው ሰራሽ መንገድ ተጨማሪ ደን ለማልማት፣ ሀገራችን ለአለም አቀፍ ማህበረሰብ ቃል የገባችበትን የተራቆተ እና የተመናመነውን የደን ሃብት መልሶ ለማልማት ማህበረሰቡን፣ የግል ሴክተሩን፣ የመንግስት ደን ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍና የአለም አቀፍ የልማት አጋሮችን ድጋፍ በማሳደግ በመካከለኛ ዘመን ዕቅድ (2016-2018) በትኩረት ይሰራል፡፡ በአጠቃላይ የአረንጓዴ አሻራ ስራን ጨምሮ በሀገራችን እየተሰሩ ያሉ የደን ልማት፣ እንክብካቤ እና ጥበቃ ስራዎች በአለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃ የሀገራችንን መልካም ገጽታና የተሰሚነት ደረጃ ከፍ እያደረጉ ስለሆነ ከምንጊዜውም በላይ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

**የልማትና ምርምር ስራዎችን ለማሳለጥ የሚያግዙ መሰረተ ልማቶች**

- የደን ሃብት ቆጠራና ልኬት ላቦራቶሪ (MRV Laboratory)
- ለውሃ እና ለአፈር ናሙናዎች ፍተሻ የሚያገለግ የተደራጀ ላቦራቶሪ፣
- የዛፍ ዘር ፊዚዮሎጂ፣ የዛፍ ዘር ጥራት እና እርጥበት ፍተሻ፣ የዛፍ ዘር በዝቅተኛ ሙቀት ማከማቻ እና የብቅለት ፍተሻ ላቦራቶሪዎች፣
- የደን ነፍሳተ ተባይ እና የደን በሽታ ጥናትና ምርምር ላቦራቶሪዎች፣
- የባዮ-ኬሚካል፣ የባዮ-ኢነርጂ እና የእንጨት ባህሪያት ጥናትና አጠቃቀም ምርምር ዎርክሾፖች፣
- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ የደን ልማት ማዕከል የሚገነባው (B+G+5) ላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ፣
- የደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ማዕከል (G+3) ላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ፣
- ጥራታቸውንና ደረጃቸውን የጠበቁ 371 ሄክታር ነባር የዘር ምንጮች፣
- 8 የምርምር ችግኝ ጣቢያዎች፣

## 4.2. የተቋሙ አደረጃጀትና የሰው ሃይል

የኢትዮጵያ የደን ልማት በአዲሱ የመንግስት ተቋማት አደረጃጀት (አዋጅ 1263/2014) መሰረት የተደራጀ የፌደራል መንግስት ተቋም ሲሆን ዓላማውም የደን ሀብታችን በዘላቂነት እንዲጠበቅ፣ እንዲለማ፣ የተራቆቱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ እና የደን ውጤቶችን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ አገራችን ከደን ሀብት የተሻለ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ስርዓተ-ምህደራዊ ጠቀሜታን እንድታገኝ በማድረግ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን በመቋቋም ለሁለንተናዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ ነው፡፡ ይህንንም ለማሳካት ተቋሙ በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 505/2014 የደን ልማት፣ ጥበቃ፣ አጠቃቀምና ምርምር እንዲሰራ ስልጣንና ሃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

ይህንን ስልጣንና ሃላፊነት መወጣት እንዲችል በዋና መስሪያ ቤትና በስሩ ባሉ ሰባት ማዕከላ 822 (550 ወንድ እና 272 ሴት) የሰው ሃይል ይዞ የተደራጀ ሲሆን አላማውንም ለማሳካት ከክልሎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሰራል (ሰንጠረዥ 3. ይመልከቱ)፡፡

### ሰንጠረዥ 3 የተቋሙ የሰው ሃይል

| ጾታ | ፒ ኤች ዲ | ሁለተኛ ዲግሪ | የመጀመሪያ ዲግሪ | ዲፕሎማ | ደረጃ 1-5 | ሰርተፍኬት | ከሰርተፍኬት በታች | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሴት | 1 | 27 | 81 | 21 | 20 | 5 | 117 | 272 |
| ወንድ | 32 | 143 | 167 | 16 | 19 | 4 | 169 | 550 |
| ድምር | 33 | 170 | 248 | 37 | 39 | 9 | 286 | 822 |

## 4.3. የተቋሙ ፋይናንስ

የኢትዮጵያ የደን ልማት ከ2016-2018 በጀት ዓመት በዕቅድ የተያዙትን የደን ልማትና ምርምር ስራዎች ለማከናወን በመደበኛና በካፒታል በጠቅላላ 2,614,437,201.10 (በካፒታል በጀት 1,919,030,000.00 ብር፣ በመደበኛ 695,407,201.10 ብር) ያስፈልገዋል፡፡

### ሰንጠረዥ 4. ከ2016-2018 በጀት ዓመት ለኢትዮጵያ ደን ልማት የሚስፈልግ በጀት

| የበጀት ዓይነት | ከ2016-2018 የሚያስፈልግ በጀት | 2016 | 2017 | 1018 |
|---|---|---|---|---|
| መደበኛ | 695,407,201.10 | 210,092,810.00 | 231,102,091.00 | 254,212,300.10 |
| ካፒታል | 1,919,030,000.00 | 1,919,030,000.00 | | |
| ድምር | 2,614,437,201.10 | 2,129,122,810.00 | 231,102,091.00 | 254,212,300.10 |

### ምቹ ሁኔታዎች

- መንግስት ለደን ዘርፍ የሰጠው ትኩረት ከፍተኛ መሆኑ፣
- የአረንጓዴ አሻራ ኢኒሼቲብ መላ ህ/ሰቡን በማሳተፍ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ፣
- በሀገራችን ተለያይነት ያለው ስርዓተ-ምህዳር መኖር፣
- የደን ዕፅዋትን ለማልማት እና ምርቱንም በብዛት ለሀገር ውስጥ እና ለዓለም ገበያ ለማቅረብ ከፍተኛ የሆነ እምቅ አቅም መኖሩ፣
- በመንግስት የሚሰሩ የአረንጓዴ ልማት ዕቅድ የሚያሳኩ ሰፋፊ የመሠረተ ልማት ሜጋ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፣

- በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የተከለሰ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ (Updated NDC) ውስጥ የደኑ ዘርፍ ዋነኛ ምሰሶ ሆኖ መቀመጡ፣
- በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚመጣውን ተፅዕኖ ለመመከት የህበረተሰባችን ግንዛቤ እያደገ መምጣቱ፣
- ደን ለአየር ንብረት ለውጥ ማስተስረይ እና ማጣጣም ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ አለም አቀፍ ትኩረት እያገኘ መሆኑ፣
- በዘርፉ ሊያሠሩ የሚችሉ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎች መኖራቸው፣
- ለዘርፍ ልማት ስራዎች የሚደረጉ አለም አቀፍ ድጋፎች እየጨመሩ መምጣታቸዉ፣

**ተግዳሮቶች**

- በክልሎችና ከዚያ በታች ባለ የአስተዳደር እርከን ወጥና የተጠናከረ መዋቅራዊ አደረጃጀት አለመኖር፣
- በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት እየጨመረ የመጣ የደን እሳት፣ የደን ተባይና በሽታ ክስተት፣
- የደን እሳትን መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችል ቴክኖሎጂና በሙያው የሰለጠነ የሰው ሃይል አለመኖር፣
- የምርምርና የልማት ስራዎችን ለማከናወን የበጀት ዕጥረት መኖሩ፣
- በግንባታ ዕቃዎች ዕጥረትና ዋጋ መናር ምክንያት ግንባታዎች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መጠናቀቅ አለመቻላቸው፡፡

## 4.4. ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎችና ስትራቴጂክ ግቦች

### 4.4.1. ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎች

ተቋሙ በህግ የተሠጠውን ስልጣንና ተግባር፣ ያሉትን እሴቶች፣ ጥንካሬዎች እና ድክመቶች፣ መልካም አጋጣሚዎችንና ስጋቶችን በመተንተን የሚከተሉት ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተዋል፡፡

1. ዘላቂ የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና አጠቃቀም፣
2. ችግር ፈቺ የደን ምርምር፣
3. ተቋማዊ አቅም ግንባታ፣
4. የደን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስርዓተ-ምህዳራዊ ጠቀሜታ፣
5. የአረንጓዴ አሻራ ስራዎች፣

### 4.4.2. ስትራቴጂካዊ ግቦችና ዋና ዋና ተግባራት

አስራ ሁለት ግቦች ተቀርፀው በግቦች ስር የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በተስማሚ የአፈጻጸም አመልካቾች፣ መለኪያዎችና የዕቅድ ዘመኑ ኢላማዎች የተዋቀሩ ሲሆን ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

የኢትዮጵያ ደን ልማት የተመረጡትን የትኩረት መስኮች መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የተገለፁት አስራ ሁለት ስትራቴጀያዊ ግቦች ተለይተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 4. የኢትዮጵያ ደን ልማት ስትራቴጂያዊ ግቦች**

| ዕይታ | ስትራቴጂክ ግቦች | ክብደት በ% |
|---|---|---|
| ተገልጋይ (20 %) | ግብ 1. የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ | 20 |
| ፋይናንስ (15%) | ግብ 2. የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ | 10 |
| | ግብ 3. የሀብት ግኝትን ማሳደግ | 5 |
| የውስጥ አሰራር (40%) | ግብ 4. ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ጤታማነት ሻሻል | 6 |
| | ግብ 5. የደን ህግ ተከባሪነት ማጎልበት | 5 |
| | ግብ 6. አገራዊ የደን ሽፋንን ማሳደግ ፣ | 7 |
| | ግብ 7. የደን ሃብት ለኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ማሳደግ፣ | 5 |
| | ግብ 8. የመረጃና ቴክኖሎጂ ማመንጨትና ማላመድ | 7 |
| | ግብ 9. የመረጃና ቴክኖሎጂ ትውውቅና ሽግግርን ማሳደግ | 5 |
| | ግብ 10. የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ | 5 |
| መማርና እድገት (25%) | ግብ 11. የዘርፉን የመሰረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ፣ | 15 |
| | ግብ 12. የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፣ | 10 |

**ግብ 1፡- የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ**

በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎቶች በመስጠት የተገልጋይ እርካታ ከ 84 % ወደ 90% የማሳደግ ስራ ይሰራል፡፡

**ግብ 2፡- የሃብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ፣**

በፋይናንስ የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት 100% በጀት እና ቁሳዊ ሃብት ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፣ በየበጀት ዓመቱ የውስጥ ኦዲት ይከናወናል፡፡

**ግብ 3፡- የሃብት ግኝት ማሳደግ**

የተለያዩ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ስራዎችን ለማካሄድ አጋዥ የሆኑ የውጭ ሀገር የድጋፍ ምንጮችን መለየትና ግንኙነት መፍጠር፣ ለደን ልማት ጥበቃ እና አጠቃቀም ዙሪያ ሀብት የሚያስገኙ ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀትና ለድጋፍ ሰጪዎች በማቅረብ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 60 ሚሊዮን ዶላር እንዲሰበሰብ ይሰራል፡፡

**ግብ 4፡- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል**

በደን መጨፍጨፍ ምክንያት የሚከሰተውን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት በመቀነስ እና ተጨማሪ ደን በማልማት እስከ ዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 33 ሚ.ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ (MtCO2eq.) የመቀነስና የማግለል ስራ ይሰራል፤ በአስራ ሁለት አለም አቀፍ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ መድረኮች በመሳተፍ የሃገሪቱን የደን ጥቅም የማስጠበቅ ስራ ይሰራል፡፡

**ግብ 5፡- የደን ህግ ተከባሪነት ማረጋገጥ፣**

- ሶስት የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ እንዲተገበር ይደረጋል፣
- ለ7.5 ሚሊዮን ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ ዘዴዎች ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ይሰራል፡፡
- በደን ሃብት ላይ የሚደርሱ ዋና ዋና ጥፋቶችና ህገወጥ እንቅስቃሴዎች ያሉባቸውን አካባቢዎች በመለየት አንድ ሃገራዊ መረጃ ይወጣል፡፡
- ህገወጥ እንቅስቃሴዎችን እንዲቀንሱ በየአመቱ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፣

- የደኑ ዘርፍ ለሃራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ለማሳደግ በደን ዘርፍ ለሚሰማሩ 390 ባለሀብቶች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

**ግብ.6፡- አገራዊ የደን ሽፋንን ማሳደግ**

- አገራዊ የደን ሽፋንን ከነበረበት 17 በመቶ በዕቅዱ ዘመን መጨረሻ ወደ 20 በመቶ ለማድረስ ይሰራል፡፡
- ጥራቱን የጠበቀ 1060 ቶን የዛፍ ዘር በማሰባሰብና ማሰራጨት
- 7.5 ቢሊዮን የደን ችግኞች የማፍላት፣
- በ2.4 ሚሊዮን ሄ/ር በወልና በመንግስት ይዞታ ላይ የደን ችግኝ ተከላ የማካሄድ (ከዚህ ውስጥ በ0.06 ሚሊዮን ሄ/ር ላይ የቀርቀሀ ደን እንዲለማ መደገፍ፣) ስራ ይሰራል፣
- 22.54 ሚሊዮን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን የመጠበቅ፣ የመንከባከብና በዘላቂነት የመጠቀም፣
- ለ0.6 ሚሊዮን ሄ/ር ደን የማኔጅመንት ፕላን ይዘጋጃል፣
- 3 ሚሊዮን ሄክታር የተራቆቱ መሬቶች እንዲያገግሙ ለማድረግ ይሰራል፡፡
- ለተመረጡ 13 ከተሞች የደን አያያዛቸው እንዲሻሻል የክትትልና ድጋፍ ስራ ይሰራል፣
- የደን ሽፋን ለውጡን ለማረጋገጥ የደን ሽፋን ስሌት ይሰራል፤
- 0.3 ሚ/ሄ/ር ላይ የጥምር ደን ግብርና ስራ እንዲካሄድ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡

**ግብ 7፡- የደን ሀብት ለኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ማሳደግ፣**

- 6 ሚሊዮን ቶን የደን ምርት እንዲመረትና ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ይደረጋ፣
- ደንና የደን ተረፈ ምርቶች 0.6 ሚሊዮን ቶን ከሰል በተሻሻለ ዘዴ እንዲመረት ይደረጋል፡፡
- 1.19 ሚ/ን ሄ/ር መሬት ላይ የሚገኙ የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ ደኖችን በአዲስ መልክ በአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ስር እንዲታቀፉ ይደረጋል፡፡
- 2.28 ሚ/ን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን በአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ስር ታቅፈው እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡

- 1 የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት የመለየት እና ዋጋ መተመን ስራ ይሰራል፣
- 84 ሚሊዮን ዶላር ከደን ምርት ውጤት ኤክስፖርት እና ከውጭ የሚገባ የደን ምርት በሃር ውስጥ በመተካት እንዲገኝ ይሰራል፣
- 900 ሚሊየን ብር ከደን ሀብት ምርት ዝውውር ሮያሊቲ እንዲሰበሰብ የክትትልና ድጋፍ ስራ ይሰራል፣
- ለ0.9 ሚሊየን ዜጎች በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ዙሪያ የስራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ድጋፍና ክትትል የማድረግ ስራ ይሰራል፣

**ግብ 8፡- በደን ምርምር ቴክኖሎጂና መረጃ ማመንጨት እና ማላመድ፣**

- የሰው ሰራሽ ደን ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የጥምር ደን ግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ፣ የተራቆቱ ተፋሰሶችንና የወንዝ ዳርቻዎችን እንዲያገግሙ ለማድረግ፣ የደን ተባይ እና በሽታ ሥርጭት እና የሚያደርሰውን ጉዳት ለማጥናትና ችግሩን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እና በተለያዩ የዛፍ ዝርያዎች የዘር ባህርያት ላይ ምርምር በማካሄድ 48 የምርምር ውጤቶችን ለማውጣት ይሰራል፡፡

- የተፈጥሮ ደኖችን በዘላቂነት ለመጠቀም እና ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ዓመታዊ የዕድገት መጠናቸውን ለማጥናት፣ መልሰው እንዲያገግሙ ለማድረግ፣ ተስማሚ ዝርያዎችን ለመምረጥ፣ የዛፍ ዝርያዎች ስብጥር መረጃ ለማውጣት፣ የተመረጡ የዛፍ ዝርያዎች አበባ እና የፍሬ ወቅት ማጥናት፣ የደን ሽፋን ለውጥና መንስዔዎችን ለመለየት፣ የወራሪና መጤ የዛፍ ዝርያዎችን ሥርጭትና ያስከተሉትን ጉዳት ለማጥናት፣ የደን ቃጠሎን መንስዔዎችንና መከላከያ ዘዴዎችን ለመለየት፣ የካርቦን ክምቸትና ተለዋዋጭነት ለማጥናት፣ ከደኑ ሴክተር የሚወጣውን የበካይ ጋዝና የካርቦን ልቀት ለመገመትና ለመተንበይ የሚያስችል ሞዴል ለማዘጋጀት፣ የአየር ንብረት ለዉጥ በተፈጥሮ ደኖች ላይ የሚያስከተለዉን ተጽዕኖ ለማወቅ የሚያስችል ምርምር በማካሄድ 23 የምርምር ውጤቶች ለማውጣት ይሰራል፡፡

- እንጨት የሆኑ እና እንጨት ያልሆኑ የደን ውጤቶችን ባህሪያት ለማጥናት፣ የተሻሻለ የደን ውጤቶችን አመራረት እና አጠቃቀም ለመለየት፣ አዳዲስ ምርቶችን ለማዘጋጀት፣ እስታንዳርድ ለማዘጋጀት፣ ለታዳሽ የሃይል ምንጭ የሚውሉ የደን ሀብቶችን ለመለየት፣ የደን ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት ለማሻሻል፣ የእንጨትን የጭረት ባህሪያት በማጥናት ለፐልፕና ወረቀት፣ ለግግር ቦርዶች ምርቶች ሊውሉ የሚችሉ የዛፍ ዝርያዎችን ለመለየት፣ እንጨትና እንጨት ካልሆኑ የደን ሀብት የሚገኙ የኬሚካል ይዘት በመለየት ለኢንዱስትሪ

ጠቀሜታ የሚውሉ ንጥረ-ነገሮችን ምርትና ምርታማነት ለማሻሻል ምርምር በማካሄድ 34 የምርምር ውጤቶች ለማውጣት ይሰራል፡፡

- በደን ዘርፍ ያሉ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ላይ ጥናትና ትንተና ማካሄድ፣ የደን ምርት ለአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን አስተዋጽኦ እና የደኑ ዘርፍ ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ማጥናት፣ የደን ኢንቨስትመንት የሚመለከቱ ጥናቶችን ማድረግ፣ የዕሴት ሰንሰለትን ማሻሻል፣ የዓለምአቀፍ የካርበን ግብይት ስርዓትን በማጥናት እና የስርዓተ-ምህዳር ግልጋሎት ዋጋን ለመተመን የሚረዳ ሞዴል ለማውጣት የሚያስችሉ ምርምሮችን በማካሄድ 18 የምርምር ውጤቶች ለማውጣት ይሰራል፡፡

**ግብ 9፦ የመረጃና ቴክኖሎጂ ትውውቅና ሽግግርን ማሳደግ**

- ለ152 የምርምር ውጤቶች የትግበራ ፓኬጅ ይዘጋጃል፣
- 120 የምርምር ውጤቶች በታወቁ ጆርናሎች ላይ እንዲታተሙ ይደረጋል፣
- ለ600 ተጠቃሚዎች በምርምር የወጡ ቴክኖሎጂዎች ቅድመ ማስፋፋት ስልጠና ይሰጣል፣
- 36 መረጃዎች በተለያዩ ሚዲያ አማራጮች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

**ግብ 10፦ የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ**

- ለ0.75 ሚሊዮን ዜጎች (50% የሴቶችንና የወጣቶችን) የስራ ዕድል ለመፍጠር ይሰራል፣
- 3 የህፃናት ማቆያ ማዘጋጀትና አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ይሰራል፣
- የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች በተመለከተ 6 የግንዛቤ ማስጨበጫ የስልጠና መድረኮች ይዘጋጃሉ፡፡
- በደን ልማትና የምርምር ስራዎች ሴቶችና ወጣቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትኩረት ይሰራል፣

## ግብ 11፡- የዘርፉን መሰረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ

- የደን ዉጤቶች ኢኖቬሽን G+3 ላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ ህንፃ እና የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል ላቦራቶሪ ኮምፕክስ G+5 ህንፃ ግንባታ ስራዎችን 100% እንዲጠናቀቁ ይሰራል፣
- 3 የተቋሙን አሰራሮች (የሰው ሃብት፣ ግዥ እና ዕቅድና ክትትል) አውቶሜት የማድረግ ስራ ይሰራል፣
- 1 ሞዴል ችግኝ ጣቢያ ማቋቋም፣
- 6 የዛፍ ዘር ምንጮችን ማቋቋም፣
- 8 ነባር የምርምር ችግኝ ጣቢያዎች ማጠናከር፣
- 371 ሄክታር ነባር የዘር ምንጮችን የመንከባከብና የማስተዳደር ስራዎች ይሰራሉ፣

## ግብ 12፡- የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፣

- ለ1650 ለሰራተኞች እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የአጭር ጊዜ ስልጠና ይሰጣል፣
- 9 የልምድ ልውውጥ ይካሄዳል፣
- ለ24 ሰራተኞች የረጅም ጊዜ ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
- የረጅም ጊዜ ስልጠና ላይ ለሚገኙ የተቋሙ ሰራተኞችም ክትትልና ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ሰንጠረዥ 5. የዘርፉ ልማት ከ2016 — 2018 በጀት ዓመት ዕቅድ ዋና ዋና ግቦች፤አመልካቾችና ኢላማዎች

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2015 | የ3 ዓመት መድረሻ ኢላማ (2016 - 2918) | 2016 | 2017 | 2018 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ግብ 1. የተገልጋዮች እርካታን ማሳደግ | | | | | | |
| | ያደገ የተገልጋይ እርካታ | በመቶኛ | 84 | 90 | 86 | 88 | 90 |
| | ግብ 2. የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ | | | | | | |
| | ጥቅም ላይ የዋለ በጀት ድርሻ | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | የተደረገ የውስጥ ኦዲት ክትትል | በቁጥር | 4 | 12 | 4 | 4 | 4 |
| | የኦዲት ግኝቶች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ የማስተካከያ መርሃ ግብር | በቁጥር | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 |
| | ግብ 3. የሀብት ግኝትን ማሳደግ | | | | | | |
| | ከአጋር ሀገሮች እና ድርጅቶች የተገኘ የፋይናንስ ድጋፍ | በሚሊየን ዶላር | 30 | 60 | 20 | 20 | 20 |
| | ግብ 4 ፦ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ማሻሻል | | | | | | |
| | ከደን ዘርፍ የቀነሰ የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት መጠን | በሚ/ሜ/ቶን | 7 | 33 | 9 | 11 | 13 |
| | ተሳትፎ የተደረገባቸው አለም አቀፍ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ መድረኮች | ቁጥር | 2 | 12 | 4 | 4 | 4 |
| | ግብ 5. የደን ህግ ተከባሪነት ማረጋገጥ | | | | | | |
| | የተዘጋጁ የደን ህግ ማዕቀፎች | በቁጥር | 2 | 3 | 1 | 1 | 1 |
| | በደን ህጎች እና አፈፃፀም ላይ ግንዛቤ ያገኙ የህብረተሰብ ክፍል ብዛት፣ | በሚሊዮን ቁጥር | 2.5 | 7.5 | 2.5 | 2.5 | 2.5 |
| | የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው በደን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች ብዛት | በቁጥር | 400 | 390 | 120 | 130 | 140 |
| | ግብ 6 ፦ አገራዊ የደን ሽፋንን ማሳደግ | | | | | | |
| | የዛፍ ዘር ማሰባሰብና ማሰራጨት | ቶን | 200 | 600 | 200 | 200 | 200 |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2015 | የ3 ዓመት መድረሻ ኢላማ (2016 - 2918) | 2016 | 2017 | 2018 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በደን የተሸፈነ መሬት ድርሻ | በመቶኛ | 17 | 20 | 18 | 19 | 20 |
| | የተዘጋጁ የዛፍ ችግኞች | ቢ/ቁጥር | 3 | 7.5 | 2.5 | 2.5 | 2.5 |
| | የተጠበቀ ነባር፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ደን | በሚ/ሄ/ር | 19.2 | 22.24 | 20.02 | 21.13 | 22.24 |
| | ተከላ የሚካሄድበት መሬት | በሚ/ሄ/ር | 0.6 | 2.4 | 0.7 | 0.8 | 0.9 |
| | ያገገመ የተራቆተ የደን መሬት | በሚ/ሄ/ር | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 |
| | የቀርከሀ ደን ማልማት | በሚ//ሄ/ር | 0.02 | 0.06 | 0.02 | 0.02 | 0.02 |
| | የጥምር ደን ግብርና ስራ እንዲጎለብት የተደረገበት የመሬት ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 0.1 | 0.3 | 0.1 | 0.1 | 0.1 |
| | የቀርቀሀ ምርት ውጤቶች ማሰልጠኛ ተቋም ማቋቋም | በቁጥር | | 1 | | | 1 |
| | ሀገራዊ የደን ሀብት ቆጠራ ማካሄድ | በመቶኛ | 50 | 100 | 60 | 80 | 100 |
| | የደን ሽፋን መረጃ | በቁጥር | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 |
| | የተዘጋጀ የደን ማኔጅመንት ፕላን | በሚ/ሄ/ር | 0.2 | 0.6 | 0.2 | 0.2 | 0.2 |
| | የደን አያያዝ እንዲሻሻል ክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸው ከተሞች ብዛት | በቁጥር | 5 | 13 | 5 | 4 | 4 |
| | **ግብ 7. የደን ሀብት ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተውን ጠቀሜታ ማሳደግ፣** | | | | | | |
| | ነባር የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 2.28 | 3.06 | 2.28 | 2.78 | 3.12 |
| | አዲስ የአሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ የተደረገለት የተፈጥሮ ደን ስፋት | ሄ/ር (ሚሊዮን) | 0.2 | 1.19 | 0.5 | 0.34 | 0.35 |
| | ከሰው ሰራሽ ደንና ከደን ተረፈ ምርቶች በተሻሻለ ዘዴ የተመረተ ከሰል መጠን | ሚሊ/ቶን | 0.2 | 0.6 | 0.2 | 0.2 | 0.2 |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2015 | የ3 ዓመት መድረሻ ኢላማ (2016 - 2918) | 2016 | 2017 | 2018 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የቀረበ የደን ምርት መጠን | ቶን (ሚሊዮን) | 1.02 | 6 | 2 | 2 | 2 |
| | በደን ዘርፍ ስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ዜጎች ብዛት | በሚሊዮን ቁጥር | 0.25 | 0.9 | 0.3 | 0.3 | 0.3 |
| | ሥርዓተ ምህዳሮች የሚያመነጩትን አገልግሎት ዋጋ ትመና የሚያሳይ መረጃ፣ | በቁጥር | 1 | 1 | | 1 | |
| | ከደን ሮያሊቲ የተገኘ ሀብት መጠን | በሚሊዮን ብር | 250 | 900 | 300 | 300 | 300 |
| | ከደን ምርት ኤክስፖርት የተገኘ እና በሃገር ውስጥ የደን ምርት ምክንያት የዳነ የውጭ ምንዛሪ መጠን | በሚሊዮን ዶላር | 20 | 84 | 27 | 28 | 29 |
| | **ግብ 8. የደን መረጃና ቴክኖሎጂ ማመንጨትና ማላመድ** | | | | | | |
| | በምርምር የወጡ ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች | | 43 | 123 | 39 | 39 | 45 |
| | • በሰው ሰራሽ ደን ምርምር | በቁጥር | 15 | 48 | 15 | 15 | 18 |
| | • በተፈጥሮ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ምርምር | በቁጥር | 13 | 23 | 7 | 8 | 8 |
| | • በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር | በቁጥር | 9 | 34 | 10 | 10 | 14 |
| | • ፖሊሲና ሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር | በቁጥር | 6 | 18 | 7 | 6 | 5 |
| | **ግብ 9. የመረጃና ቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ** | | | | | | |
| | የተዘጋጁ የምርምር ውጤቶች የትግበራ ፓኬጅ ብዛት | | 41 | 152 | 50 | 51 | 51 |
| | • በሰው ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን | በቁጥር | 13 | 46 | 15 | 15 | 16 |
| | • በተፈጥሮ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ | በቁጥር | 13 | 47 | 15 | 16 | 16 |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2015 | የ3 ዓመት መድረሻ ኢላማ (2016 - 2918) | 2016 | 2017 | 2018 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | • በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን | በቁጥር | 8 | 31 | 10 | 10 | 11 |
| | • ፖሊሲና ሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር | በቁጥር | 7 | 28 | 9 | 9 | 10 |
| | በታወቁ ጆርናሎች ላይ የታተሙ የምርምር ውጤቶች | በቁጥር | 22 | 120 | 40 | 40 | 40 |
| | በሰው ሰራሽና ጥምር ግብርና ደን | በቁጥር | 9 | 41 | 13 | 13 | 15 |
| | በተፈጥሮ ደን እና የአየር ንብረት ለውጥ | በቁጥር | 7 | 35 | 11 | 11 | 13 |
| | በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን | በቁጥር | 3 | 22 | 7 | 7 | 8 |
| | ፖሊሲና ሶሽዮ-ኢኮኖሚክስ ምርምር | በቁጥር | 3 | 22 | 7 | 7 | 8 |
| | ለተጠቃሚዎች በቴክኖሎጂ ቅድመ ማስፋፋት የተሰጠ ስልጠና | በተሳታፊ ቁጥር | 200 | 600 | 200 | 200 | 200 |
| | በተለያዩ የሚዲያ ቻናሎች ተደራሽ የተደረገ መረጃ ብዛት | በቁጥር | 12 | 36 | 12 | 12 | 12 |
| | **ግብ 10 የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ** | | | | | | |
| | የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሴቶች እና ወጣቶች ድርሻ | በሚሊዮን ቁጥር | 0.188 | 0.375 | 0.125 | 0.125 | 0.125 |
| | የተዘጋጀ የህፃናት ማቆያ | በቁጥር | 2 | 3 | 1 | 1 | 1 |
| | የሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶች አካቶ የተሰጠ ሥልጠናዎች ብዛት | በቁጥር | 2 | 6 | 2 | 2 | 2 |
| | **ግብ 11 ፡- የመሠረተ ልማት ሽፋን ማሳደግ** | | | | | | |
| | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ማዕከል G+5 ላቦራቶሪ ግንባታ ስራ ያለበት ደረጃ | በመቶኛ | 25 | 100 | 100 | | |

| ተ.ቁ | የዘርፍ አመልካቾች | መለኪያ | መነሻ 2015 | የ3 ዓመት መድረሻ ኢላማ (2016 - 2918) | 2016 | 2017 | 2018 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የደን ዉጤቶች እኖቬሽን ማዕከል ላቦራቶሪ ኮምፕሌክስ G+3 ግንባታ ስራ ያለበት ደረጃ | በመቶኛ | 45.13 | 100 | 100 | | |
| | አውቶሜት የተደረጉ የተቋሙን አሰራሮች | በቁጥር | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 |
| | አዲስ የተቋቋሙ የዛፍ ዘር ምንጮች | በቁጥር | | 6 | 2 | 2 | 2 |
| | እንክብካቤ የተደረገላቸው ነባር የዛፍ ዘር ምንጮች | በሄ/ር | 371 | 371 | 371 | 371 | 371 |
| | አዲስ የተቋቋሙ ሞዴል የምርምር ችግኝ ጣቢያዎች | በቁጥር | | 1 | 1 | | |
| | በመካሄድ ላይ የሚገኙ የምርምር ችግኝ ጣቢያዎች ብዛት | በሄ/ር | 8 | 8 | 8 | 8 | 8 |
| | **ግብ 12 ፡- የዘርፉን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማሳደግ** | | | | | | |
| | የአጭር ግዜ ስልጠና ያገኙ ተመራማሪዎች | በቁጥር | 265 | 1650 | 550 | 550 | 550 |
| | የረጅም ግዜ ስልጠና ያገኙ ሰራተኞች | | 73 | 24 | 8 | 8 | 8 |
| | ክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸው የረጅም ግዜ ስልጠና ላይ ያሉ ሠራተኞች ብዛት | | 71 | | 71 | | |
| | ስልጠና ያገኙ አመራሮች ብዛት | ቁጥር | 60 | 60 | 60 | | |
| | የተካሄደ የልምድ ልውውጥ ብዛት | በቁጥር | 2 | 9 | 3 | 3 | 3 |

### የዕቅዱ ማስፈጸሚያ የበጀት ፍላጎት

የሶስት ዓመት እቅዱን ለማሳካት የደን ልማትና የምርምር ስራዎችን ለማከናወን፣ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለማሟላት፣ በግንባታ ላይ ያሉ ሁለት የላቦራቶሪ ህንፃዎችን ጨምሮ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች፣ የደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ማዕከል ዎርክሾፕ ማሽኖችና መሳሪያዎች፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት እና ሌሎች ግብዓቶችን ለመሟላት የሚያስፈልግ በጀት ከፌደራል መንግስት ግምጃ ቤት እና ከልማት አጋሮች የሚገኝ ድጋፍን ግምት ውስጥ በማስገባት በጠቅላላው 2,614,437,201.10 ብር በካፒታልና በመደበኛ በጀት እንደሚያስፈልግ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በየዓመቱ የሚያስፈልፈው በጀት በሰንጠረዥ 2 ተመላክቷል፡፡

**ሰንጠረዥ 7 የዕቅዱ ማስፈጸሚያ የበጀት ፍላጎት**

| የበጀት ዓይነት | ከ2016-2018 የሚያስፈልግ በጀት | 2016 | 2017 | 1018 |
|---|---|---|---|---|
| መደበኛ | 695,407,201.10 | 210,092,810.00 | 231,102,091.00 | 254,212,300.10 |
| ካፒታል | 1,919,030,000.00 | 1,919,030,000.00 | | |
| ድምር | 2,614,437,201.10 | 2,129,122,810.00 | 231,102,091.00 | 254,212,300.10 |

## 5. በዕቅድ ዘመኑ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የአደጋ ስጋቶች እና የመቋቋሚያ ስልቶች

በዕቅድ ዘመኑ የተያዙ ግቦችን ለማሳካትና የሚጠበቁ ውጤቶችን ለማምጣት ሊያስራ የሚችል ተቋማዊ አደረጃጀት፣ የተሟላ የሰው ሃይል፣ በቂ ሃብት፣ እና ለደን ልማት እና ምርምር አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች አቅርቦት፣ ምቹ የስራ አካባቢ፣ ሰላም እና ደህንነት ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ ሆኖም ግን ባለው ተጨባጭ አገራዊና ነባራዊ ሁኔታ በዕቅድ ዘመኑ የተያዙትን ግቦች በአስተማማኝ መልኩ ለመፈፀም ማነቆ ሊሆን ይችላሉ ተብለው የተለዩ ስጋቶች ከዚህ ቀጥሎ በተገለፀው ሰንጠረዥ የቀረቡ ሲሆን እነዚህ ስጋቶች የዕቅድ አፈፃፀሙን እንዳያደናቅፉ እንዲሁም የልማት ግቦቹ በውጤታማነት እንዲፈፀሙ ለማስቻል ስጋቶቹን የመቋቋሚያ ስልቶች ከወዲሁ ታቅደው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 8. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች እና የመቋቋሚያ ስልቶች**

| ስጋቶች | የመቋቋሚያ ስልቶች |
|---|---|
| በአገር አቀፍ ደረጃ የመሬት አጠቃቀም ህጎችና ደንቦች ያለመዘጋጀትና አለመተግበራቸው፣ | የመሬት አጠቃቀም ህጎችና ደንቦች እንዲዘጋጁና በአግባቡ እንዲተገበሩ ግፊት ማድረግ |
| የበጀት እጥረትና የዘመናዊ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ውስንነት፣ | ከልማት አጋር አካላት በሚገኙ ድጋፎች ተጨማሪ ሃብት እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት ማሳደግ |
| ከልማት አጋሮች የሚገኘው ድጋፍ በቂ እና ተገማች አለመሆን | በአለም አቀፍ የድርድር መድረኮች በመሳተፍ የፋይናንስ ፣ የአቅም ግንባታ እና የቴክኖሎጂ ድጋፍ በማስገኘት የሀገራችንን ጥቅም ማሥጠበቅ |
| በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች እና ተጽእኖዎች | ከተቋሙ ውጪ ካሉ ተቋማት፣ የዘርፉ ባለድርሻ አካላትና ከህብረተሰቡ ጋር በቅንጅት መስራት፣ |
| በምርምር የወጡ መረጃና ቴክኖሎጂዎችን ወደ ተጠቃሚ ለማድረስ የሚያግዝ ስርዓትና አደረጃጀት በሚፈለገዉ ደረጃ አለመኖር ፣ | በምርምር የሚወጡ ቴክኖሎጂ እና መረጃ ፓኬጆችን ለተጠቃሚ ለማድረስ እስከ ታችኛው እርከን የኤክስቴንሽን አደረጃጀት እንዲዘረጋ ማድረግ፣ በተጨማሪም በተቋሙ የሚከናወኑ የቅድመ ማስፋፋት ሥራዎችን አጠናክሮ መሥራት |

| ስጋቶች | የመቋቋሚያ ስልቶች |
|---|---|
| ከውጭ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎች እና የላቦራቶሪ ግብዓቶችን በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት በተፈለገው ጊዜ ማግኘት አለመቻሉ፣ | ከልማት አጋሮች ጋር በትብብር በመሠራት የቴክኖሎጂዎች እና የላቦራቶሪ ግብዓቶችን አቅርቦት ማሳደግ |
| የደንን ሰደድ እሳት፣ በሽታ እና ተባይ እና ወራሪ መጤ አረም መስፋፋት | የዱር ሰደድ እሳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት መዘርጋት እና ተቋማዊ እና ሀገራዊ አቅም መፍጠር |
| የተቋሙ የምርምር ጣቢያዎችና የዘር ማመንጫ ደኖች በተደጋጋሚ ለጥቃት መዳረጋቸው እና በአካባቢው ህበረተሰብ ያልተገባ የባለቤትነት ጥያቄዎች ፈተና ውስጥ መግባታቸው | ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመወያየት የምርምር ይዞታዎች ሕጋዊ ከለላ እንዲያገኙና እንዲከበሩ ማድረግ<br><br>ተቋሙ በይዞታዎቹ ላይ በሚያካሂዳቸው የምርምር ስራወዎች ስራ በመፍጠር ህብረተሰቡን ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ |
| በእንጨት ቴክኖሎጂ፣ በደን በሽታና ነፍሳት ተባዮች፣ በደን ስርጸት፣ በደን ጄኔቲክስ፣ በአካባቢ ምህንድስና/ቴክኖሎጂ ወዘተ የሰለጠነ የሰው ሃይል /ተመራማሪዎች/ ከገበያው ላይ በበቂ ሁኔታ ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑ | ከተቋሙ ውጪ ካሉ ተቋማትና ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት መስራት፤<br><br>በተጠቀሱት ዘርፎች ባለሞያዎችን በበቂ ሁኔታ ለማፍራት እንዲቻል ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር የትምህርት ክፍሎቹ እንዲከፈቱ ውይይት ማድረግ እና የተመራማሪዎችንና ባለሙያዎችን ብቃት ማሳደግ፤ |
| በተፈጥሮ ደን ላይ ጥገኛ ሆኖ ኑሮውን የሚመራ የህብረተሰብ ክፍል የተፈጥሮ ደኑን አማራጭ የሃይልና የገንዘብ ምንጭ አድረጎ በመጠቀሙ ቀጣይነት ባለው የደን ሃብት አያያዝ ላይ እንቅፋት መሆኑ፤ | ደን አምራች አርሶ-አደሮች እንዲስፋፉ ከፍተኛ የቴክኖሎጂና የምክረ-ሃሳብ ድጋፍ ማድረግ፤ |

## 6. የዘርፉ ዕቅድ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት

በዘርፉ ዕቅድ ትግበራ ሂደት ተግባራዊ የሚሆነዉ የአፈፃፀም ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ሥርዓት በዋናነት በብሄራዊ ፕላን ሚንስቴር ተዘጋጅቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀዉና ከጥር 1 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በመሆን ላይ የሚገኘዉን ብሄራዊ የዕትዕ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስረዓት አፈጻጸም መመሪያን ማዕከል አድርጎ የሚፈጸም መሆኑ እንደ ተጠበቀ ሆኖ በዘርፍ ደረጃ ውጤታማ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት የዘርፉን የ3 ዓመት የልማት ዕቅድ ለመከታተልና፣ ለመገምገም፣ የተዘጋጁ መርሐግብሮችና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ደረጃ ለማሻሻል እንዲሁም የሚጠበቁ ውጤቶች መምጣታቸውን ለማረጋገጥ ዋነኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪም በዕቅድ አስፈፃሚ እና ፈፃሚ አካላት ዘንድ የግልፀኝነት እና የተጠያቂነት አሰራር በማስፈን ድክመቶች እንዲታረሙና ጥንካሬዎች እንዲጎለብቱ ይደረጋል፡፡ ስለዚህም ዘርፉ ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ከተግባሪ አካላት ጋር ትስስርና ተመጋጋቢነት በሚፈጥር መልኩ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት አቅጣጫና አተገባበር ሂደት አዘጋጅቷል፡፡

### የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ይዘቶች፣

### የተቀናጀ፣ የተደራጀ፣ ተመጋጋቢ እና ተደጋጋፊ አሠራርን ማረጋገጥ፣

የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሪፖርት ፎርማት እና የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ በወጥነት ተፈፃሚ መሆን እንዳለባቸው ታሳቢ ተደርጓል፡፡ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜም የዘርፉን የአምስት አመት፣ የአመት፣ የስድስት ወርና የሩብ አመት የአፈፃፀም ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማቅረብ ይሆናል፡፡

የሚዘጋጁ ዘገባዎች በእቅድ ዘመኑ በየአመቱና በእቅድ ዘመኑ የመጨረሻ አመት ሊደረስባቸው የሚገባ ቁልፍ የውጤት መስኮች (Key Result Areas) እና የሴክተር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች (Key Performance Indicators) መሠረት በማድረግ የሚከናወን ነው፡፡

## ግልፅኝነትንና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ፣

አስተማማኝና ወጥ የመረጃ ሥርዓት መዘርጋትና አሳታፊ እንዲሆን የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ይህም የሚረጋገጠው የክልሎችና የዘርፎች አፈፃፀም ወጥ መስፈርትን መሠረት በማድረግ የስራ ክፍፍል የሚደረግ እና ተጠያቂነትን እንዲሰፍን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡ ክትትልና ግምገማው የሴቶችና የወጣቶች እኩል ተጠቃሚነት ተሳታፊነትን ያረጋግጣል፤ የአገልግሎት ተጠቃሚዎች መረጃ በፆታና በዕድሜ በየእርከኑ የመለየት፣ የመሰብሰብ፣ የመተንተንና ሪፖርት የማድረግ ስርዓት ይጠናከራል፡፡

## የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በታቀደው መሠረት መፈፀማቸውን በየደረጃው ማረጋገጥ

በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የሚከናወኑ የተለያዩ የልማት ፕሮግራሞችና ኢንቨስትመንቶች የአካባቢ ሁኔታና ደህንነት ባረጋገጠ መልኩ እንዲከናወኑ ለማስቻል የሥራ ግንኙነት ይጠናከራል፣ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ የቢሮ እና የመስክ ክትትልና ግምገማ በማድረግ ግብረ መልስ እንዲሰጥ ይደረጋል፣ ከመደበኛ ሪፖርቶች ጥናቶችና ከመስክ ጉብኝቶች በተገኘው መረጃ ላይ በመመርኮዝ የተለዩ ክፍተቶችን እና መሰናክሎችን የሚያስተካክሉ ድጋፎች ይደረጋሉ፡፡ የልማት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ የሆኑ ህበረተሰብ ክፍሎችን የመስክ ምልከታና ግብረ መልስ አሰጣጥ ሂደት አካል እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

## ጠቃሚ ትምህርቶችን መውሰድ እና ተሞክሮዎችን መቀመር፣

መስረያቤቱ ከሃገርና ዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች ጋር ያለውን የስራ ግንኙነት የማጠናከር፣ የግሉን ዘርፍ ተሳታፊነት ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር የመከተል፣ ህብረተሰቡን በእቅዶቹና በአተገባበር ላይ ተሳታፊነታቸውን የማረጋገጥ፣ እንዲሁም በየአካባቢው የሚገኙ መልካም ተሞክሮዎችን እንዲቀመሩና እንዲሰፉ ይደረጋል፣ ለባለድርሻ አካላት ስለ ዘርፉ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ሕጎች በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ በማድረግ በዘርፉ የሚኖራቸውን ሚና በማጎልበት የፖሊሲውንና የሕጎችን ተፈፃሚነት የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል፡፡

### የክትትልና ግምገማ አቅምን መገንባት

የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ የሚያስተባብረዉን የሥራ ክፍል መዋቅራዊ አደረጃጀት በማሻሻል በሰው ኃይል፣ በአሰራር ሥርዓት እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሙሉ ቁመና ያለውና ተልዕኮውን በአግባቡ መወጣት የሚችል እንዲሆን ማድረግ፣ በየደረጃው ተግባራዊ የሚደረግ አሳታፊ፣ ግልፅና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ የሚያስችል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ተቋማዊ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ፣ በፈፃሚው፣ በመካከለኛና በከፍተኛ አመራሩ ደረጃ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ የውጤት ተኮር ዕቅድ፣ የድጋፍና ክትትል ሥርዓት ዝርጋታና ትግበራን ክህሎት ሊያስድጉ የሚችሉ ተከታታይ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን በመስጠት የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ግንባታ ሥራ ይሠራል፡፡

ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ከተግባሪ አካላት ጋር ቋሚና መደበኛ የአፈፃፀም ግምገና የምክክር መድረኮችን ከማካሄድ በተጨማሪ ወቅታዊ የድጋፍና የክትትል ሥራዎች ይከናወናሉ፣ በኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ለፕላንና ልማት ሚንስቴር እንዲሁም ለግብርና ሚኒስትር በሚቀርቡ ወቅታዊ ሪፖርቶች ላይ የሚሰጡ ግብረ መልሶችን እንደ አጋዥ መሳሪያ በመጠቀም በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ማከናወን የታሰበ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ይሆናል፡፡

## 8. ማጠቃለያ

በዕቅድ ዘመኑ ተቋማዊ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በመስራት፣ ለዕቅዱ ማስፈፀሚያ የሚስፈልገውን ሰብዓዊ እና ቁሳዊ አቅምን በመገንባት የሚያስፈልጉ የልማት እና የምርምር ግብዓቶችን በየደረጃው በማሟላት ዘላቂ የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ፣ እንክብካቤና አጠቃቀም ተግባራትን እና ችግር ፈቺ የደን ምርምር ስራዎችን በማከናወን፣ በዕቅድ የተያዙ ግቦችን እና ዋና ዋና ተግባራትን በውጤታማነት በመፈፀምና በየበጀት ዓመቱ የሚጠበቁ ውጤቶች በሚፈለገው መጠን እና ጥራት በማስገኘት የደን ሀብታችን በዘላቂነት እንዲጠበቅ፣ እንዲለማ፣ የተራቆቱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ እና የደን ውጤቶችን ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ፣ አገራችን ከደን ሀብት የተሻለ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊ እና ስርዓተ-ምህደራዊ ጠቀሜታን እንድታገኝ ለማስቻል እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን በመቋቋም ለሁለንተናዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

ይህንንም በውጤታማነት ለመፈፀም ከክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች እንዲሁም በዘርፉ አብረው ከሚሰሩ የልማት አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት መስራት፣ በየደረጃው ያሉ አመራሮች እና ፈፃሚዎች ቁርጠኝነትና የታቀዱ ግቦች እንዲሳኩ እና በየበጀት ዓመቱ የሚጠበቁ ውጤቶች በሚፈለገው መጠን እና ጥራት እንዲገኙ ለማስቻል ተረባርቦ መስራት ይጠበቃል፡፡ አፈፃፀሙንም በየወቅቱ በመከታተልና የፊዚካልና የፋይናንስ አፈፃፀም በየደረጃው ወቅቱን ጠብቆ በመገምገም በበጀት ዓመቱ የሚጠበቁ ውጤቶች በዕቅዱ መሰረት መከናወናቸውን በማረጋገጥና ተገቢውን የአፈፃፀም ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ስራዎች ይከናወናሉ፡

## 9. አባሪ

| የኢትዮጵያ ደን ልማት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የፕሮግራም አይነት | 2013 | | 2014 | | 2015 | | |
| | ዓመታዊ በጀት | ጠቅላላ ወጪ | ዓመታዊ በጀት | ጠቅላላ ወጪ | ዓመታዊ በጀት | የ6 ወር እቅድ | የ6 ወር ጠቅላላ ወጪ |
| ፕሮግራም 1፡- የአስተዳደርና ስራ አመራር | 41,520,269.40 | 41,458,091.49 | 44,967,145.21 | 43,355,617.16 | 36,274,017.33 | 20,525,960.02 | 20,236,824.08 |
| ፕሮግራም 2.፡- የደን ምርምር ፕሮግራም | 70,494,866.29 | 68,690,695.02 | 76,959,657.05 | 70,918,698.68 | 63,210,272.88 | 33,210,849.86 | 28,231,538.44 |
| ፕሮግራም 3፡- የደን ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ፕሮግራም | 105,800,000.00 | 92,475,213.75 | 109,473,576.00 | 107,221,924.00 | 84,252,442.67 | 57,148,058.72 | 54,134,804.01 |
| **ድምር** | **217,815,135.69** | **202,624,000.26** | **231,400,378.26** | **221,496,239.84** | **183,736,732.88** | **110,884,868.60** | **102,603,166.53** |

| የኢትዮጵያ ደን ልማት | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ፕሮግራም | ንዑስ ፕሮራም | የ2016-2018 የበጀት ወጪ | | | | የፋይናንስ ምንጭ | | | |
| | | | 2016 | 2017 | 2018 | ድምር | መንግስት | የተቋም ገቢ | ዕርዳት | ብድር |
| 1 | የአስተዳደር ና ስራ አመራር ፕሮግራም | | 51,303,446.00 | 56,433,790.60 | 62,077,169.66 | 169,814,406.26 | 169,814,406.26 | | | |
| 2 | የደን ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ፕሮግራም | የተፈጥሮ ደን ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ | 78,371,827.50 | 86,209,010.25 | 94,829,911.28 | 259,410,749.03 | 259,410,749.03 | | | |
| | | የደን ሀብት ጥናት እና ምዝገባ | 5,371,827.50 | 5,909,010.25 | 6,499,911.28 | 17,780,749.03 | 17,780,749.03 | | | |
| | | አረንጓዴ አሻራና ሰው ሰራሽ ደን ልማት፣ | 4,467,877.00 | 4,914,664.70 | 5,406,131.17 | 14,788,672.87 | 14,788,672.87 | | | |
| | | የደን ውጤቶች አጠቃቀምና ስርዓት ተከባሪነት | 3,234,407.00 | 3,557,847.70 | 3,913,632.47 | 10,705,887.17 | 10,705,887.17 | | | |
| 3 | የደን ምርምር ፕሮግራም | | 67,343,424.08 | 74,077,766.49 | 81,485,543.14 | 222,906,733.70 | 222,906,733.70 | | | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | | **210,092,809.080** | **231,102,089.988** | **254,212,298.987** | **695,407,198.055** | **695,407,198.055** | | | |

| የኢትዮጵያ ደን ልማት | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የፕሮግራም | ንዑስ ፕሮግራም | ውጤት | የ2016-2018 የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ኢላማዎች (በብር) | | | | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | | |
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | ድምር(2016-2018) | የክልል በጀት | የክልል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | የፌደራል በጀት | የፌደራል የልማት ድርጅት ፋይናንስ | ዕርዳት | ብድር (የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ) | የግል ፋይናንስ | የግል-መንግስት ሽርክና ፋይናንስ |
| 1 | የአስተዳደርና ስራ አመራር | | የተሰጠ ድጋፍና አገልግሎት | 51,303,446.00 | 56,433,790.60 | 62,077,169.66 | 169,814,406.26 | | | 169,814,406.26 | | | | | |
| 2 | የደን ልማት ጥበቃና እንክብካቤ ፕሮግራም | የተፈጥሮ ደን ልማት፣ ጥበቃና እንክብካቤ | የተፈጥሮ ደን እንዲለማ እንዲጠበቅና እንክብካቤ እንዲደረግለት የተካሄደ ድጋፍና ክትትል | 78,371,827.50 | 86,209,010.25 | 94,829,911.28 | 259,410,749.03 | | | 259,410,749.03 | | | | | |
| | | የደን ሀብት ጥናት እና ምዝገባ | የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ደኖችን የተሻሻለ የደን አያያዝ እቅድ ስርዓት እንዲኖራቸው፣ ሀገራዊ የደን ሀብት ቆጠራ እንዲካሄድ እነዲሁም ከደን ዘርፍ የሚለቀቁ | 5,371,827.50 | 5,909,010.25 | 6,499,911.28 | 17,780,749.03 | | | 17,780,749.03 | | | | | |

| የኢትዮጵያ ደን ልማት | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የፕሮግራም | ንዑስ ፕሮግራም | ውጤት | የ2016-2018 የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ኢላማዎች (በብር) | | | | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | |
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | ድምር(2016-2018) | የክልል በጀት | የክልል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | የፌደራል በጀት | የፌደራል የልማት ድርጅት ፋይናንስ | ዕርዳት | ብድር (የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ) | የግል ፋይናንስ | የግል-መንግስት ሽርክና ፋይናንስ |
| | | | የሙቀት አማቂ ጋዞች ቅነሰ ልኬት መረጃ እንዲዘጋጅ የተካሄደ ክትትልና ድጋፍ | | | | | | | | | | | | |
| | | አረንጓዴ አሻራና ሰው ሰራሽ ደን ልማት፣ | ሰው ሰራሽ ደን እንዲለማ እንዲጠበቅና እንክብካቤ እንዲደረግለት ለክልሎች የተካሄደ ድጋፍና ክትትል | 4,467,877.00 | 4,914,664.70 | 5,406,131.17 | 14,788,672.87 | | | 14,788,672.87 | | | | | |
| | | የደን ውጤቶች አጠቃቀምና ስርዓት ተከባሪነት | ከደን ዘርፍ ክሮያሊቲ፣ ከደን ምርት ውጤቶች ሽያጭ፣ በስራ ዕድል፣ ተገቢውን ጥቅም ማግኘት እንዲያስችል በክልሎች የተደረገ ክትትልና ድጋፍ፣ | 3,234,407.00 | 3,557,847.70 | 3,913,632.47 | 10,705,887.17 | | | 10,705,887.17 | | | | | |

| የኢትዮጵያ ደን ልማት | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የፕሮግራም | ንዑስ ፕሮግራም | ውጤት | የ2016-2018 የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ኢላማዎች (በብር) | | | | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | | |
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | ድምር(2016-2018) | የክልል በጀት | የክልል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | የፌደራል በጀት | የፌደራል የልማት ድርጅት ፋይናንስ | ዕርዳት | ብድር (የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ) | የግል ፋይናንስ | የግል-መንግስት ሽርክና ፋይናንስ |
| 3 | የደን ምርምር ፕሮግራም | | በሰው ሰራሽ ደን ምርምር የወጡ የምርምር ውጤቶች | 18,891,377.00 | 20,780,514.70 | 22,858,566.17 | 62,530,457.87 | | | 62,530,457.87 | | | | | |
| | | | በተፈጥሮ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ምርምር የወጡ የምርምር ውጤቶች | 21,440,139.60 | 23,584,153.56 | 25,942,568.92 | 70,966,862.08 | | | 70,966,862.08 | | | | | |
| | | | በደን ውጤቶች ኢኖቬሽን ምርምር የወጡ የምርምር ውጤቶች | 16,079,225.00 | 17,687,147.50 | 19,455,862.25 | 53,222,234.75 | | | 53,222,234.75 | | | | | |
| | | | በፖሊሲ ሶሺዮ ኢኮኖሚክስ ምርምር የወጡ የምርምር ውጤቶች | 9,532,682.48 | 10,485,950.73 | 11,534,545.80 | 31,553,179.01 | | | 31,553,179.01 | | | | | |
| | | | የደን ልማት ፋሲሊቲ | 1,400,000.00 | 1,540,000.00 | 1,694,000.00 | 4,634,000.00 | | | 4,634,000.00 | | | | | |
| **ድምር** | | | | **210,092,809.08** | **231,102,089.99** | **254,212,298.99** | **695,407,198.05** | **-** | **-** | **695,407,198.05** | | | | | |

| የኢትዮጵያ ደን ልማት | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ፕሮጀክት | የ2016-2018 የበጀት ወጪ | | | | የፋይናንስ ምንጭ | | | |
| | | 2016 | 2017 | 2018 | ድምር | መንግስት | የተቋም ገቢ | የውጭ ዕርዳት | ብድር |
| 1 | በኢትዮጵያ ደን ልማት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ላቦራቶሪ ሕንጻ ግንባታ | 1,492,160,000.00 | | | 1,492,160,000.00 | 1,492,160,000.00 | | | |
| 2 | በኢትዮጵያ ደን ልማት የእንጨት ቴክኖሎጂ ላቦራቶሪ ሕንጻ ግንባታ | 426,870,000.00 | | | 426,870,000.00 | 426,870,000.00 | | | |
| | **ድምር** | **1,919,030,000.00** | | | **1,919,030,000.00** | **1,919,030,000.00** | | | |

| የኢትዮጵያ ደን ልማት | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የፕሮግራም ዝርዝር | የፕሮጀክቶች ዝርዝር | እስከ 2015 የነበረ የኢንቨስትመንት ወጪ (በብር)* | የ2016-2018 የኢንቨስትመንት ፍላጎትና ኢላማዎች (በብር) | | | | ከ2018 በኃላ የኢንቨስትመንት ወጪ (በብር)** | የፋይናንስ ምንጭ | | | | | | | | |
| | | | 2016 | 2017 | 2018 | ድምር (2016-2018) | | የክልል በጀት | የክልል ልማት ድርጅት ፋይናንስ | የፌደራል በጀት | የፌደራል የልማት ድርጅት ፋይናንስ | ዕርዳት | ብድር (የውጭ ወይም የሀገር ውስጥ) | የግል ፋይናንስ | የግል-መንግስት ሽርክና ፋይናንስ |
| ካፒታል | በኢትዮጵያ ደን ልማት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ላቦራቶሪ ሕንጻ ግንባታ | 27,787,534.00 | 1,492,160,000.00 | | | 1,492,160,000.00 | | | | 1,492,160,000.00 | | | | | |
| | በኢትዮጵያ ደን ልማት የእንጨት ቴክኖሎጂ ላቦራቶሪ ሕንጻ ግንባታ | 58,775,447.00 | 426,870,000.00 | | | 426,870,000.00 | | | | 426,870,000.00 | | | | | |
| **ድምር** | | **86,562,981.00** | **1,919,030,000.00** | | | **1,919,030,000.00** | | | | **1,919,030,000.00** | | | | | |